# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## 5ኛ ክፍል



የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር

# ለመጽሐፉ ሊደረግ ስለሚገባው የአያያዝ ጥንቃቄ



ይህን መጽሐፍ ብዙ ተማሪዎች ስለሚገለገሉበት በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባዋል፡፡ የሚከተሉት 10 ነጥቦች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዞ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ሃሳብ ይሰጣሉ፡፡

1. የመጽሐፉን ሽፋን በጠንካራ ወረቀት ወይንም በላስቲክ መሸፈን፡፡
2. መጽሐፉን ርጥበት በሌለበት ደረቅ ቦታ ላይ በጥንቃቄ ማስቀመጥ፡፡
3. መጽሐፉን በቆሻሻ እጅ ያለማገላበጥና ገፆቹን ያለመግለጥ፡፡
4. በመጽሐፉ የሽፋንም ሆነ የውስጥ ገፆች ላይ አላስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችንና ጽሑፎችን ያለመሳልና ያለመጻፍ፡፡
5. ለመጽሐፉ የገጽ መለያ ወይንም የንባብ ማረፊያ የሆነ እልባት በጠንካራ ክርታስ ሠርቶ መጠቀም እንጂ የቆሙበትን ቦታ ለማስታወስ ገፆቹን ደጋግሞ ያለማጠፍ፡፡
6. ከመጽሐፉ ውስጥ አንድም ገጽ ሆነ ስዕል ገንጥሎ አለማውጣት፡፡
7. መጽሐፉ ቢገነጠል እንኳ በጥንቃቄ መልሶ በማጣበቂያ ማስተሽ ማያያዝ፡፡
8. መጽሐፉ ቦርሳ ውስጥ ሲከተት እንዳይታጠፍና እንዳይጨማደድ ጥንቃቄ ማድረግ፡፡
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው በውሰት ሲሰጥ የተዋሰው ሰው በጥንቃቄ እንዲይዝ መንገር፡፡
10. መጽሐፉን በጥንቃቄ መግለጥ፣ ገፆቹ እንዳይገነጠሉና እንዳይወይቡ በጥንቃቄ መያዝ፡፡

# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

## 5ኛ ክፍል

አዘጋጅ፡- ፕሪን ኢንተርናሽናል አማካሪ ድርጅት

ጸሐፊ፡- ወ/ት ፀዳለ ጉደታ

የቴክኒካል አማካሪዎች፡- ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ

አርታኢ፡- አቶ የሻው ተሰማ

ግራፊክስ ዲዛይን፡- አቶ ፍቃደእግዚአብሄር ከበደ

የምልክት ቋንቋ ስዕል፡- አቶ ካሌብ በለጠ

ሌሎች ስዕሎች፡- አቶ አሰፋ ጉታ

አስተባባሪዎች፡- ዶ/ር ጥላዬ ካሣሁን፣ ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር

# ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ ---------- | 3 |
| ምዕራፍ አንድ፡ | |
| ቤተሰብ (10 ክፍለ ጊዜያት) ---------- | 4 |
| ምዕራፍ ሁለት፡ | |
| ንጽህናን መጠበቅ (10 ክፍለ ጊዜያት) ---------- | 11 |
| ምዕራፍ ሦስት፡ | |
| አካባቢያችን (10 ክፍለ ጊዜያት) ---------- | 17 |
| ምዕራፍ አራት፡ | |
| የትራፊክ ደኅንነት (12 ክፍለ ጊዜያት) ---------- | 23 |
| ምዕራፍ አምስት፡ | |
| የዱር እንስሳት (9 ክፍለ ጊዜያት) ---------- | 30 |
| ምዕራፍ ስድስት፡ | |
| ባህል (8 ክፍለ ጊዜያት) ---------- | 36 |
| ምዕራፍ ሰባት፡ | |
| ጎጂ ልማዶች (12 ክፍለ ጊዜያት) ---------- | 42 |
| ምዕራፍ ስምንት፡ | |
| ባህላዊ ጨዋታዎች (8 ክፍለ ጊዜያት) ---------- | 48 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ፡ | |
| ተረት (9 ክፍለ ጊዜያት) ---------- | 53 |
| ምዕራፍ አስር፡ | |
| ተውኔት (9 ክፍለ ጊዜያት) ---------- | 59 |

# መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀው ለአምስተኛ ክፍል የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ (ኢምቋ) ማስተማሪያ መጽሐፍ አጋዥ እንዲሆን ታስቦ ነው፡፡ መምሪያው ልዩ ልዩ ተግባራትን፣ ቴክኒኮችን፣ ብልሃቶችንና በኢምቋ መማር - ማስተማር ሥራ ውስጥ መሠረት የሚጥሉ ጉዳዮችን ያካተተ በመሆኑ፣ ተማሪዎችን በትምህርታቸው ውጤታማ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ በመምሪያው ውስጥ የተነደፉት የማስተማሪያ ዘዴዎችም ለመማር-ማስተማር መስተጋብር አዎንታዊ ሥነ ምሕዳር በመፍጠር፣ ለተማሪዎቹ ቋንቋ እድገት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ ይታሰባል፡፡

መምሪያው ተማሪዎች በተዋጣ ሁኔታ እንዲማሩ ከማገዝ ባሻገር፣ መምህራን የኢምቋን መጽሐፍ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ሲያስተምሩ፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመጠቆም የመማር ማስተማሩን ሂደት የተመቻቸ እንዲሆን ያግዛል፡፡

የመምህር መምሪያው የመማሪያ መጽሐፉን 10 ምዕራፎች መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ በየምዕራፉ መጀመሪያ ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣ የትምህርቱ ይዘትና የትምህርቱ አቀራረብ ዘዴ በግልጽ ተመልክተዋል፡፡ መምህራንም ይህንኑ በመገንዘብ፣ ትምህርቱን ሲያቀርቡ፣ ሂደቱን ከይዘቶቹ ጋር የተጣጣመ ለማድረግና የትምህርቱንም አቀራረብ እንደ ሁኔታው እያላዘቡ ውጤቱን ፍሬያማ ለማድረግ መምሪያው ያግዛል፡፡ የየምዕራፉ የትምህርት ይዘቶችም መምህራን በቀላሉ እንዲገነዘቡዋቸው ሆነው ስለቀረቡ፣ የክፍል ተግባራትን በአግባቡ ለማቀድ ያለ ጥርጥር ይረዳቸዋል፡፡

የመምህር መምሪያው፣ መምህራን አንድን ምዕራፍ በማስተማር ላይ እያሉ፣ እንዲሁም አስተምረው ከጨረሱ በኋላ፣ ተማሪዎችን እንዴት መመዘን እንዳለባቸው በመጠቆም የምዘና ብልሃቶችንም ያመላክታቸዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች የምዕራፉን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱት እየገመገመ፣ ያሉበትን ሁኔታ ለመረዳት እንዲቻል፣ ከዚያም መምህራን እንዴት ግብረ መልስ መስጠት እንደሚገባቸው አቅጣጫ ይሰጣል፡፡

በመሆኑም፣ መምህራን እነዚህን ነጥቦች በአንክሮ በመመልከትና ከተማሪው መማርያ መጽሐፍ ጋር በማቀናጀት፣ የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ መጣር ይጠበቅባቸዋል፡፡ የትምህርቱ ውጤታማነት በሌላ ገጹ የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋንም እድገት ለማጠናከርና ለማስፋፋት፣ አዳዲስ ሃሳቦችንም ለማፍለቅና ለማጎልበት የበኩሉን ሚና መጫወቱ የማይታበል ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# ቤተሰብ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ስለቤተሰብ አባላት ምንነት ለይተው በኢምቋ ያስረዳሉ፡፡
- በቤተሰብ መካከል ያለ ዝምድናን ለይተው በኢምቋ ይገልፃሉ፡፡
- ዝምድና አመልካች ቃሎችን በኢምቋ ይናገራሉ፡፡
- ከቤተሰብ አባላትና ዝምድና ጋር የተያያዙ የቁልፍ ምልክቶች እሴቶችን ያብራራሉ፡፡
- በኢምቋ በማንበብ ይረዳሉ፡፡
- ስለቤተሰብ አባላት የሙያ ዓይነት የሚገልፁ ዐረፍተ ነገሮችን በኢምቋ ይመሠረታሉ፡፡
- የተጓደሉ (ያላለቁ) ዐረፍተ ነገሮችን እያሟሉ ይጽፋሉ፤ የራሳቸውንም ዐረፍተ ነገሮች ይመሠርታሉ/ ያስረዳሉ፡፡

## ይዘት

- ◊ ከዝምድና ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶች
- ◊ የቤተሰብ አባላት ምንነት
- ◊ የቤተሰብ አባላትና የሙያ ዓይነት
- ◊ ቤተሰብን የሚያመለክቱ ስሞችና የዝምድና መግለጫዎች
- ◊ የቤተሰብ አባላት ዝምድናዎች አገላለጽ
- ◊ የዝምድና መግለጫ ምልክቶች
- ◊ የቤተሰብን ሁኔታ የሚገልፁ ዓረፍተ ነገሮች

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡-** 10

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት፣ ትምህርቱን ከመጀመርዎ በፊት ማነቃቂያ እንዲሆን መሪ/መነሻ ጥያቄ በኢምቋ ይጠይቁ፡፡ ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ፡፡

በተማሪው መጽሐፍ በምዕራፉ ውስጥ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን ተግባራት፣ ዕይታዊ ንባብን የሚያጎለብቱ ሥዕላዊ መግለጫዎችንና ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡

በተማሪው መጽሐፍ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ቤተሰብ አባላትና ዝምድና የሚያወሳውን ምንባብ በኢምቋ በማንበብ፣ ተማሪዎች በትኩረትና በማስተዋል መከታተላቸውን ይቆጣጠሩ/ ይከታተሉ፡፡ ተማሪዎችም በቡድን እየሆኑ ምንባቡን በየተራ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ምንባቡንም ምን ያህል እንደተረዱ ለማወቅ ስለራሳቸው ቤተሰብ ይጠይቋቸው፡፡

ምንባቡን መሠረት በማድረግ፣ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን መልመጃዎች እንደመመሪያቸው ሁኔታ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ያሠሯቸው፡፡ ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጡዋቸው፡፡

ለውይይት ዕድል የሚፈጥሩ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በኢምቋ ይጠይቁ፡፡ ቤተሰብንና ዝምድናን የሚያሳዩ የተለያዩ ሥዕሎችን ወይም ምስሎችን እንዲያዩና በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች ተራ በተራ ስለቤተሰባቸው አባላት እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡ የተማሪዎቹንም አገላለፅ እንደ ምሳሌ በመጠቀም አንድ ሐሳብ በተለያየ መንገድ እንደሚገለፅ ለተማሪዎች በኢምቋ ያስረዱ፡፡ ተማሪዎች ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁ ያበረታቱ፡፡ በክፍለ ጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ የቁልፍ ምልክቶችን አቻ ቃሎቻቸውን በሰሌዳው ላይ በመጻፍና በኢምቋ በማሳየት ማጠቃለያ ክለሳ ያድርጉላቸው፡፡

## ማሳሳቢያ

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም የሐሳብ ልውውጥ ለማከናወን በኢምቋ ይጠቀሙ።

## ቁልፍ ምልክቶች፡-

**ሀ) ዝምድና፡-** ቤተሰብ፣ አክስት፣ አጎት፣ ቅድመ አያት፣ አማት (የሚስት ወይም የባል እናት ወይም አባት)፣ አማች፣ (የልጅ ወይም የእኅት ባል ወይም የሚስት ወንድም)፣ ምራት (የወንድ ልጅ ሚስት)፣ ዋርሳ (ለወንድም የወንድም ሚስት ወይም የባል ወንድም)፣ አይት (የባል እህት)፣ እንጀራ እናት፣ እንጀራ አባት፣ እንጀራ ልጅ፣ የወንድም ልጅ፣ የእህት ልጅ፣ የአጎት ልጅ፣ የአክስት ልጅ፣ አበልጅ፣

**ለ) ተግባር፡-** ሙያ፣ ሠራተኛ፣ የቤት እመቤት፣ ጡረተኛ. . . ወዘተ.

## ማብራሪያ፡-

**ቤተሰብ፡-** ቤተሰብ የኅብረተሰብ መሠረት ነው። ቤተሰብ ባልና ሚስት በመረዳዳት፣ ዘር በመተካትና ልጆችን በግብረገብ ኮትኩቶ በማሳደግ የሚመሰርቱት ማህበራዊና ሕጋዊ ተቋም ነው።

አባት ወይም እናት ወይም ሁለቱም አብረው የቤተሰቡ የበላይ አስተዳዳሪዎች ሲሆኑ፣ ለልጆች አስፈላጊውን ክብካቤና ድጋፍ ያደርጋሉ። ልጆች ደግሞ ወላጆቻቸውን ሊያከብሩና ሊታዘዙ ይገባል።

| ዝምድና ገላጭ ቃሎች | መግለጫ |
|---|---|
| ቅድመ አያት (ሴት/ወንድ) | የአያት እናትና አባት |
| አያት (ሴት/ወንድ) | የእናትና አባት ወላጆች |
| አባት/እናት | ወላጆች |
| አክስት | የእናት ወይም የአባት እኅት |
| አጎት | የእናት ወይም የአባት ወንድም |
| አማች | የልጅ ወይም የእኅት ባል ወይም የሚስት ወንድም |
| ምራት | የወንድ ልጅ ሚስት |
| አማት | የሚስት ወይም የባል እናት ወይም አባት |
| ዋርሳ | ለወንድም የወንድም ሚስት ወይም የባል ወንድም |
| አይት | የባል እህት |
| ልጅ | የእናትና የአባት ሴት ወይም ወንድ ልጅ |
| አበልጅ | አንዱ የሌላውን ሰው ልጅ ክርስትና ሲያነሳ በመካከል የሚፈጠር የዝምድና ዓይነት |
| እንጀራ እናት | ባል ከሌላ ሴት ለወለደው ልጅ እንደ ሁለተኛ እናት የምትቆጠር |
| እንጀራ አባት | ባል ከሌላ ሴት ለወለደው ልጅ እንደ ሁለተኛ አባት የሚቆጠር |
| እንጀራ ልጅ | ባል ወይም ሚስት ከውጭ ወይም ከሌላ ሰው የወለዱት ልጅ |

ከዚህ በታች በምሕረት ቤተሰቦች ዙሪያ የቀረበውን የቤተሰብ አባላትና ሙያቸውን ለተማሪዎች በማንበብ በመማሪያው መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎችን ያሰሯቸው፡፡

*ስለ ቤተሰብ አባላትና ሙያቸው የሚገልጽ አጭር ፅሁፍ*

## የምሕረት ቤተሰብ

አቶ አበበ የምሕረት ወንድ አያት ናቸው፡፡ እሳቸውም ጡረተኛ ናቸው፡፡

ወይዘሮ ብርቄ የምሕረት ሴት አያት ናቸው፡፡ እሳቸውም የቤት እመቤት ናቸው፡፡

መሠረት የምሕረት አክስት ናት፡፡ እሷም ነጋዴ ናት፡፡

በቀለ የምሕረት አጎት ነው፡፡ እሱም ግንበኛ ነው፡፡

ተስፋዬ የምሕረት አባት ነው፡፡ እሱም ጠበቃ ነው፡፡

ሐና የምሕረት እናት ናት፡፡ እሷም መምህር ናት፡፡

ሙሉ የምሕረት አማት ናት፡፡ እሷም ጸሐፊ ናት፡፡

ሕይወት የምሕረት የአጎት ልጅ ናት፡፡ እሷም ነርስ ናት፡፡

ከበደ የምሕረት ወንድም ነው፡፡ እሱም ሙዚቀኛ ነው፡፡

መኮንን የምሕረት ባል ነው፡፡ እሱም ፓይለት ነው፡፡

ዮሐንስ የምሕረት የወንድም ልጅ ነው፡፡ እሱም የአጸደ ሕፃናት ክፍል ተማሪ ነው፡፡

ዐረፍተ ነገር፡- ዓረፍተ ነገር ማለት ሙሉ ስሜትን ሊሰጥ የሚችል በስርዓት የተቀነባበሩ የቃላት ወይም የሐረጎችን ስብስብ ነው፡፡

ሐተታዊ ዐረፍተ ነገር፡- አዎንታዊ ወይም አሉታዊ  የሆነ መልዕክት ለማስተላፍ ስንፈልግ የምንመሠርተው ዐረፍተ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡- (ሃና እርስሳስ ገዛች፡፡ (አዎንታዊ)

ከበደ ደብተር አልገዛም፡፡ (አሉታዊ)

ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገር፡- ይህን ዓረፍተ ነገር ጥያቄ ለማቅረብ ስንፈልግ የምንጠቀምበት ዓረፍተ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡- (አልማዝ ስንት ዓመትሽ ነው? ከማን ጋር ትኖራለህ?)

ትዕዛዛዊ ዐረፍተ ነገር፡- ትዕዛዝ ለማስተላለፍ ስንፈልግ የምናዋቅረው ዐረፍተ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡- (በሩን ዝጉ፡፡ ቤቱን አፅዱ፡፡)

## መርጃ መሣሪያ

ፎቶዎች/ምስሎች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች/ሰንጠረዦች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ የኢምቋ መዝገበ-ምልክት፡፡

## ግምገማ

- ◊ የቤተሰብ አባላት ምንነትን ለይተው በኢምቋ ማስረዳታቸውን ይመልከቱ፡፡
- ◊ የቤተሰብ አባላትንና ዝምድናን የሚያሳይ ሥዕልን በኢምቋ ማብራራት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ◊ የተጓደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በአግባቡ በመሙላት በኢምቋ ማሳየት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
- ◊ የቤተሰብ አባላትን ሙያ በድራማ መልክ ለማሳየት መሞከራቸውን ይመልከቱ፡፡
- ◊ የቤተሰባቸውን አባል ስም በኢምቋ መናገር/ማሳየት መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- ◊ ከዝምድና ጋር ተያይዘው ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ተገቢ መልስ በኢምቋ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ◊ በኢምቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ይገምግሙ፡፡
- ◊ በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልዕክቶችን በኢምቋ ማብራራት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
- ◊ ዝምድናን አመልካች ቃሎችን በኢምቋ መናገራቸውን/ማሳየታቸውን ይከታተሉ፡፡
- ◊ የዝምድና መግለጫ ምልክቶችንና ቃሎችን ማቀናጀት መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡

## የምዕራፍ አንድ መልመጃዎች መልስ

# ትምህርት ሁለት

### መልመጃ አንድ

1. አንድ
2. ሁለት
3. የመጨረሻ
4. ስድስት
5. ልጅ
6. የግርማ እናት፣ አክስቱ እና እህቱ
7. የግርማ የወንድሙ ሚስት እና አክስቶቹ
8. አባቱ፣ አጎቱ እና የእህቱ ባል

### መልመጃ ሁለት፡ ተቃራኒ

1. እህት
2. አባት
3. ሴት አያት
4. አጎት
5. ወንድ
6. የእንጀራ እናት

## መልመጃ ሶስት፡ ተመሳሳይ

1. የወንድ ልጅ ሚስት
2. የእናት ወይም የአባት እኅት
3. የአያት እናትና አባት
4. የእናት ወይም የአባት ወንድም
5. ለወንድም  የወንድም ሚስት  ወይም የባል ወንድም
6. የልጅ ወይም የእኅት ባል ወይም የሚስት ወንድም

# ትምህርት አራት

## መልመጃ አንድ

1. የምህረት አክስት፤ ስራዋ ንግድ
2. ሐና፤ስራዋ መምህርነት
3. የምህረት አጎት፤ ስራው ግንበኛ
4. ሕይወት፤ ስራዋ ሰዓሊ
5. የምህረት ወንድም፤ስራው ሙዚቀኛ

## መልመጃ ሁለት

1. አጎት
2. አክስት
3. አያት
4. አክስት
5. ወንድም
6. አጎት
7. አያት
8. እህት
9. አይት
10. ዋርሳ
11. ቅድመ አያት
12. ምራት

# ምዕራፍ ሁለት

# ንፅህናን መጠበቅ

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ስለ ጽዳትና ንጽሕና ምንነት በኢምቁ ይገልፃሉ፡፡
- የግልና የአካባቢን ንጽሕናን ካለመጠበቅ የሚመጡ ችግሮችን በኢምቁ ያስረዳሉ፡፡
- የግል ንጽሕናን ለመጠበቅ መደረግ የሚገባቸው ነገሮች ላይ በኢምቁ ይወያያሉ፡፡
- የአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅን በተመለከተ በኢምቁ ይናገራሉ፡፡
- ንጽሕናን አለመጠበቅ የሚያመጣውን ችግር በዝርዝር በኢምቁ ይገልፃሉ፡፡
- እራሳችሁን ከንጽሕና ጉድለት ከሚመጡ በሽታዎች ይጠብቃሉ፡፡
- የግልና የአካባቢ ንጽሕና ያላቸውን ተያያዥነትና ልዩነት በኢምቁ ይገልፃሉ፡፡
- በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልእክቶችን በኢምቁ ያብራራሉ፡፡
- ከአራት ቃል/ምልክት በላይ የያዙ ዓረፍተ ነገሮችን በኢምቁ ይመሰርታሉ፡፡
- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃሎችን በኢምቁ ይጠቀማሉ፡፡
- የጎደሉ ዓረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቁ ይሰራሉ፡፡

## ይዘት

◊ የግልና የአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ

◊ ንጽሕናን አለመጠበቅ የሚያመጣው ችግር

◊ የግል ንጽሕና አጠባበቅ ተግባራት

◊ ስለ ጽዳት ሊኖረን የሚገባ አመለካከት

◊ ከንጽሕና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች

◊ የግልና የአካባቢ ንጽሕና ያላቸው ተያያዥነትና ልዩነት

◊ ጽዳትን የተመለከቱ፣ ገላጭ ስሞችና ግሶች

◊ ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡-** 10

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት፣ የዕለቱን፣ ትምህርት ማነቃቂያና መሪ/መነሻ ጥያቄ በኢምቋ በመጠየቅ ይጀምሩ:: ከርእሱ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶችንና መሠረታዊ ነጥቦችን ያስተዋውቁ::

በምዕራፉ ውስጥ በየትምርት ክፍሉ የቀረቡትን ተግባሮች፣ ዕይታዊ ንባብን የሚያጎለብቱ ስዕላዊ መግለጫዎችንና ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ እንዲሰሩ ያድርጉ::

በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ግልና አካባቢ ንጽሕና የሚያወሳውን ምንባብ ለተማሪዎች በዝግታ በኢምቋ በማንበብ ተማሪዎች በትኩረትና በማስተዋል መከታተላቸውን ይቆጣጠሩ:: ተማሪዎች ምንባቡን ተራ በተራ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲያነቡ በማድረግ የተረዱትን ሐሳብ በራሳቸው የአገላለፅ ስሜት በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ:: ምንባቡንም ምን ያህል እንደተረዱ ይጠይቋቸው::

ምንባቡን መሠረት በማድረግ፣ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን መልመጃዎች እንደመመሪያቸው ሁኔታ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ያሠሯቸው:: ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው::

ለውይይት ዕድል የሚፈጥሩና ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በጥንድ እየሆኑ እንዲወያዩ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸው:: ተራ በተራ እየወጡ ስለንጽሕና አጠባበቅ በኢምቋ እንዲያስረዱ ያድርጉ:: የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ንጽሕና በመጠበቅ፣ እራሳቸውን እንዴት ከንጽሕና ጉድለት ከሚመጡ በሽታዎች እንደሚጠብቁ በኢምቋ እንዲያስረዱ ያበረታቷቸው:: የተለያዩ የንጽሕና አጠባበቅ ተግባራትን የሚያሳዩ ሥዕሎችና /ፎቶ ግራፎችን/ በማዘጋጀት ተማሪዎቹ በጥንድና ቡድን ሆነው በኢምቋ እንዲያስረዱ ያድርጉ:: ተማሪዎች ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው:: በክፍለ ጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ የቁልፍ ምልክቶችን አቻ ቃሎቻቸውን በሰሌዳው ላይ በመጻፍና በኢምቋ በማሳየት ማጠቃለያ ክለሳ ያድርጉላቸው::

## ማሳሳቢያ

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም የሐሳብ ልውውጥ ለማከናወን በኢምቋ ይጠቀሙ፡፡

## ቁልፍ ምልክቶች፡-

**ሀ) የአካባቢ ጽዳት፡-** በሽታ፣ ጤና፣ ጠንቅ፣ (ሰበብ ወይም መዘዝ)፣ ነፍሳት፣ ብክለት፣ የአየር ብክለት፣ የውሃ ብክለት፣ የአካባቢ ብክለት፣ መፀዳጃ ቤት፣

**ለ)የግል ጽዳት፡-** እጅን መታጠብ፣ ገላን መታጠብ፣ ፀጉርን መታጠብ፣ የቤት ጽዳት፣ የጥርስ ንጽሕና፣ የልብስ ንጽሕና፣ የጥፍር ንጽሕና፣ የእግር ንጽሕና፣ የጫማ ንጽሕና

**ማብራሪያ፡-** *የግል ንጽሕናን ለመጠበቅ የሚደረጉ ተግባሮች*

| የግል ንጽሕናን ለመጠበቅ የሚደረጉ ተግባሮች | ንፅህናን ካለመጠበቅ የሚመጡ የጤና ችግሮች |
|---|---|
| ገላን መታጠብ | ሆድ መታመም |
| ፀጉርን መታጠብ | ዓይን መታመም |
| ጥፍርን ማፅዳት | ጉንፋን |
| ልብስን ማጠብ | የቆዳ በሽታ |
| ፊትን መታጠብ | |
| እግርን መታጠብ | |
| ጥርስን መቦረሽ | |

መምህር/ት፡- ስለግል ንጽሕና አጠባበቅና  የግል ንጽሕናን ካለመጠበቅ በሚመጡ ችግሮች ዙሪያ ተማሪዎችን ያወያዩ፡፡

| የአካባቢን ንፅህና ለመጠበቅ የሚደረጉ ተግባሮች | የአካባቢ ንፅህናን ካለመጠበቅ የሚመጡ ችግሮች |
|---|---|
| ግቢን ማፅዳት | የአየር መበከል |
| ቆሻሻን ሰብስቦ ማቃጠል | የውሃ መበከል |
| መንገዶችን ማጽዳት | የጤና ችግር |
| ቆሻሻን በተገቢው ሁኔታ ማስወገድ | አየር ወለድ በሽታዎች |
| | ውሃ ወለድ በሽታዎች |
| አበቦችንና ዛፎችን መትከል | በመተንፈሻ አካላት ላይ የሚከሰቱ የጤና ችግሮች |

መምህር/ት፡- ስለአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅና  የአካባቢ ንጽሕናን ካለመጠበቅ በሚመጡ ችግሮች ዙሪያ ተማሪዎችን ያወያዩ፡፡

### መርጃ መሣሪያ

ፎቶዎች/ምስሎች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች/ቻርቶች/ሰንጠረዦች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ የኢምቂ መዝገበ-ምልክት

### ግምገማ

- ስለ ጽዳትና ንጽሕና ምንነት በኢምቂ መግለፅ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የግል እና የአካባቢን ንጽሕናን ካለመጠበቅ የሚመጡ ችግሮችን በኢምቂ ማስረዳት መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- ንጽሕናን አለመጠበቅ የሚያመጣውን ችግር በዝርዝር በኢምቂ ማብራራት መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- የግል ንጽሕና አጠባበቅ ተግባራትን በኢምቂ መዘርዘር መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
- እራሳቸውን ከንጽሕና ጉድለት ከሚመጡ በሽታዎች መጠበቅ የሚችሉበትን ዘዴ በኢምቂ መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የግልና የአካባቢ ንጽሕና ያላቸውን ተያያዥነትና ልዩነት በኢምቂ መግለፅ መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
- በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልዕክቶችን በኢምቂ ማብራራት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
- ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃሎችን በኢምቂ መጠቀማቸውን ይመልከቱ፡፡

## የምዕራፍ  ሁለት መልመጃዎች መልስ

## ትምህርት ሁለት

### መልመጃ አንድ

1. የአንድ ሠፈር

2. ተስፋዬና ፅንቁ
3. ስለግል ንጽሕና
4. ንጹህ
5. ጎጂ

## መልመጃ ሁለት

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሐሰት
6. ሐሰት
7. እውነት

## መልመጃ ሶስት

1. ለ
2. መ
3. መ
4. ሐ
5. መ

## መልመጃ አራት፡ አዛምድ

1. ለ
2. መ
3. ሠ
4. ሐ
5. ሀ

# ትምህርት አራት

## መልመጃ ሁለት

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. ሐሰት
6. እውነት
7. ሐሰት
8. እውነት
9. ሐሰት
10. እውነት

# ምዕራፍ ሦስት

# አካባቢያችን

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ስለ አካባቢ ምንነት በኢምቋ ያብራራሉ፡፡
- የገጠርና የከተማ አካባቢ ገፅታዎችን ይለያሉ፡፡
- በተለያዩ አካባቢዎች ሊኖር የሚችል ልዩነትና ዝምድና በኢምቋ ይገልፃሉ፡፡
- ስለ አካባቢ ክብካቤ በኢምቋ ይናገራሉ፡፡
- በየአካባቢያቸው ስለሚከናወኑ ተግባራት ልምድ ይለዋወጣሉ፡፡
- በአካባቢ ክብካቤ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በኢምቋ ያስረዳሉ፡፡
- አካባቢያቸውን በአሁን ጊዜ ዐረፍተ ነገሮች በኢምቋ ይገልፃሉ፡፡
- የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ ይሰራሉ፡፡

## ይዘት

- ◊ በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች
- ◊ አካባቢን መጠበቅና መንከባከብ የሚያስገኘው ጠቀሜታ
- ◊ የአካባቢ፣ የቦታና፣ የተፈጥሮ ገፅታ ስሞች
- ◊ የአካባቢ አንድነትና ልዩነት
- ◊ የአካባቢ ብክለት መንስዔዎች
- ◊ የገጠርና የከተማ አካባቢ
- ◊ በአካባቢ የሚደረጉ የዕለት ተዕለት ድርጊቶች አገላለጽ
- ◊ ተመሳሳይና ተቃራኒ ምልክቶች

## የተመደበውክፍለ ጊዜ ፡- 10

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት፣ የዕለቱን ትምህርት ማነቃቂያና መሪ ጥያቄ በኢምቋ በመጠየቅ ይጀምሩ፡፡ ከአካባቢና የአካባቢ ክብካቤ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ፡፡

በምዕራፉ ውስጥ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን ተግባሮች፣ ዕይታዊ ንባብን የሚያጎለብቱ ሥዕላዊ መግለጫዎችንና ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡

በተማሪው መጽሐፍ ስለገጠርና ከተማ አካባቢ የሚያወሳውን ምንባብ ለተማሪዎች በኢምቋ በማንበብ ተማሪዎች በትኩረትና በማስተዋል መከታተላቸውን ይቆጣጠሩ፡፡ ከምንባቡ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በኢምቋ ይጠይቁ፡፡

ተማሪዎችንም በቡድን በመከፋፈል ምንባቡን በድጋሚ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ምንባቡንም ምን ያህል እንደተረዱ ይጠይቋቸው፡፡ ምንባቡንም መሠረት በማድረግ የቀረቡትን የተለያዩ መልመጃዎች እንደመመሪያቸው ሁኔታ በግልና በቡድን ያሠሯቸው፡፡ ተማሪዎች መልመጃውን ከሠሩ በኋላም ሙከራዎቻቸውን በማረም የማበረታቻና የማቃኛ አስተያየቶችን ይስጧቸው፡፡

የአካባቢ ክብካቤን፣ የገጠርና የከተማ አካባበቢን የሚያሳዩ ሥዕሎችን በማሳየት ስሜታቸውን በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስለሚከናወኑ የአካባቢ ክብካቤ ተግባራት ተራ በተራ በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡ የተለያዩ የተፈጥሮ አካባቢ ገፅታዎችን ተማሪዎች በሥዕል ሠርተው እንዲሳዩ ያድርጉ፡፡ ምንባቡን ተራ በተራ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲያነቡ በማድረግ የተረዱትን ሐሳብ በራሳቸው ኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡ ለውይይት የሚጋብዝ ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች በጥንድ

እየሆነ  በኢምቋ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

ተማሪዎች ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው፡፡ በክፍለ ጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ የቁልፍ ምልክቶችን አቻ ቃሎቻቸውን በሰሌዳው ላይ በመጻፍና በኢምቋ በማሳየት ማጠቃለያ ክለሳ ያድርጉላቸው፡፡

## ማሳሳቢያ

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም የሐሳብ ልውውጥ ለማከናወን በኢምቋ ይጠቀሙ፡፡

## ቁልፍ ምልክቶች፡-

የአየር ጠባይ፣ ብክለት፣ በሽታ፣ ጤና፣ ህብረተሰብ፣ ከተማ፣ ገጠር፣ ወንዝ፣ ባህር፣ ኩሬ፣ ምንጭ፣ ጎርፍ፣ መናፈሻ፣ ተክሎች፣ ጫካ፣ ተራራ/ተራራማ፣ ሜዳ/ሜዳማ፣ በረሀ/በረሀማ፣ እረኛ፣ በረት፣ ፎቅ

## ማብራሪያ፡-

| ስለአካባቢ ክብካቤ የሚዘረዝሩ ተግባራት | |
|---|---|
| አካባቢን እንዴት እንከባከባለን? | |
| ቆሻሻን ሰብስቦ ማቃጠል | ዛፍ መትከል |
| መንገዶችን ማጽዳት | የአፈር መሸርሸርን መከላከል |
| ቆሻሻን በተገቢው ሁኔታ ማስወገድ | ፍሳሾችን በአግባቡ ማስኬድ |

መምህር/ት፡- አካባቢን ካለመንከባከብ የተነሳ የሚመጡ ችግሮች ላይ ተማሪዎችን  በኢምቋ ያወያዩ፡፡

## መርጃ መሣሪያ

ፎቶዎች/ምስሎች፣ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮቸ/ቻርቶቸ/ሰንጠረዦች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ የኢምቋ መዝገበ-ምልክት

## ግምገማ

– የአካባቢ ምንነትን በኢምቋ መግለፅ መቻላቸውን ያረጋግጡ;;

- የገጠርና የከተማ አካባቢ ገፅታዎችን መለየት መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- ልዩ ልዩ የአካባቢ ገፅታዎችን የሚያሳዩ ሥዕሎችን በኢምቋ ማብረራት መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
- ልዩ ልዩ የአካባቢ ክብካቤ ተግባራትን በድራማ መልክ በአግባቡ በኢምቋ ማሳየት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
- በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልእክቶችን በኢምቋ ማብራራት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
- የአካባቢን ልዩነትና ዝምድና በኢምቋ የተቻላቻውን ያህል መግለፅ መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- በኢምቋ ዐረፍተ ነገር መስራት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡

## የምዕራፍ ሦስት መልመጃዎች መልስ

## ትምህርት ሁለት

### መልመጃ አንድ

1. እውነት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. ሐሰት
6. እውነት
7. እውነት
8. እውነት
9. ሐሰት
10. እውነት

## መልመጃ ሁለት

1. በክረምት
2. በረት
3. ጠባብ
4. ከምንጭ
5. ጫካ

# ትምህርት ሶስት

## መልመጃ ሁለት፡ ተመሳሳይ

1. ረ
2. ቀ
3. ለ
4. ተ
5. ሸ
6. በ
7. መ
8. ሐ
9. ሀ
10. ሠ

# ትምህርት አምስት

## ክፍል ሁለት

### መልመጃ አንድ

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት

### መልመጃ ሁለት

1. ሐ
2. መ
3. ለ
4. ሀ
5. መ

# ምዕራፍ አራት

# የትራፊክ ደኅንነት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- መሠረታዊ የትራፊክ ህጎችን በኢምቋ ያሳያሉ።
- የትራፊክ መብራት ቀለማትን ህጋቸውን በማቀናጀት በኢምቋ ይገልፃሉ።
- ስለትራፊክ ህግ አስፈላጊነት በኢምቋ ይወያያሉ።
- የትራፊክ ህግን በመጠበቅ ራሳቸውን ከትራፊክ አደጋ ይጠብቃሉ።
- በቆመ መኪና ተከልለው መንገድ መሻገር እንደሌለባቸው ይገነዘባሉ።
- የዜብራ ማቋረጫዎችን በመጠቀም መንገዶችን ይሻገራሉ።
- መሠረታዊ የትራፊክ ህጎችን በኢምቋ ያስረዳሉ።
- በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልእክቶችን በኢምቋ ያሳያሉ።
- የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ ይሰራሉ።

## ይዘት

- ◊ የትራፊክ ደህንነትና የመንገድ ስነ-ስርዓት
- ◊ በመንገድ ላይ መደረግ ስለሚገባ ጥንቃቄ
- ◊ የትራፊክ መብራት አጠቃቀም
- ◊ የትራፊክ ደህንነት አጠባበቅና አደጋን የመከላከል ዘዴ
- ◊ የትራፊክ ህግ አስፈላጊነት
- ◊ መሠረታዊ የትራፊክ ህጎች
- ◊ የስምና የግስ ገላጮችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስራት
- ◊ ከዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ገላጮችን መለየት

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡-** 12

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት፣ ትምህርቱን ከመጀመርዎ በፊት ማነቃቂያ እንዲሆን መሪ/መነሻ ጥያቄ በኢምቋ ይጠይቁ፡፡ ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ፡፡ ከርዕሱ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶችንና ጽንሰ ሐሳቦችን ያስተዋውቁ፡፡

በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን ተግባሮች፣ ዕይታዊ ንባብን የሚያጎለብቱ ስዕላዊ መግለጫዎችንና ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ እንዲሠሩ ያድርጉ፡፡

በተማሪው መጽሐፍ ስለመንገድ ላይ ትርዒት የሚያወሳውን ምንባብ በኢምቋ በማንበብ፣ ተማሪዎች በትኩረትና በማስተዋል መከታተላቸውን ይቆጣጠሩ፡፡ ተማሪዎች ምንባቡን ተራ በተራ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲያነቡ በማድረግ የተረዱትን ሐሳብ በራሳቸው የአገላለፅ ስሜት በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡ ምንባቡንም ምን ያህል እንደተረዱ ይጠይቁዋቸው፡፡

ምንባቡን መሠረት በማድረግ፣ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን መልመጃዎች እንደመመሪያቸው ሁኔታ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ያሠሩዋቸው፡፡ ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጡዋቸው፡፡

ተማሪዎች በግልና በቡድን ሆነው ምንባቡን በማንበብ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁና እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ሰዎች እራሳቸውን ከትራፊክ አደጋ ለመጠበቅ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በኢምቋ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ያመቻቹ፡፡ ከዚህ በፊት ስላጋጠማቸውና ስለሰሙት የትራፊክ አደጋዎች ለክፍል ጓደኞቻቸው በኢምቋ እንዲያስረዱ ያድርጉ፡፡ በክፍል ውስጥ የትራፊክ ህጎችን በኢምቋ እንዲለማመዱ ያመቻቹ፡፡ መሠረታዊ የትራፊክ ምልክቶችን በማሳየት ተጨማሪ ገለፃ በኢምቋ ያድርጉ፡፡

ተማሪዎች ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው፡፡ በክፍለ ጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ የቁልፍ ምልክቶችን አቻ ቃሎቻቸውን በሰሌዳው ላይ በመጻፍና በኢምቋ በማሳየት ማጠቃለያ ክለሳ ያድርጉላቸው፡፡

## ማሳሳቢያ፡-

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም የሐሳብ ልውውጥ ለማከናወን በኢምቋ ይጠቀሙ፡፡

## ቁልፍ ምልክቶች፡-


የትራፊክ መብራት ቀለማት፣ ቁም፣ ተጠንቀቅ፣ ሂድ፣ ዜብራ፣ ትራፊክ፣ ፖሊስ፣ መኪና፣ ባይስክል፣ ሞተር ሳይክል፣ ባቡር፣ የመኪና/የባቡርአደጋ፣ ተሽከርካሪዎች፣ የእግረኛ መንገድ፣ መስቀልኛ መንገድ፣ አደባባይ፣ ድልድይ፣ መሸጋገሪያ፣ አስፋልት/የመኪና መንገድ፣ የባቡር ሃዲድ

## ማብራሪያ፡-

*የተሽከርካሪና የእግረኛ ማስተላለፊያ የትራፊክ መብራቶች ቀለማትና ህጋቸው*

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ የትራፊክ መብራቶች ቀለማትና ህጋቸው | |
|---|---|---|
| | የመብራት ቀለም | ህግ |
| 1 | ቀይ | ለእግረኛ ማቋረጫ የተሰመረውን መስመር ሳያልፉ መቆም፡፡ |
| 2 | ቀይና ቢጫ | ቆመው የነበሩ ለመሄድ መዘጋጀት፡፡ |
| 3 | አረንጓዴ | ወደ መረጡት አቅጣጫ መጓዝ፡፡ |
| 4 | ቢጫ | መስቀለኛ መንገድ መሀል የገቡ በፍጥነት መውጣት፤ በመግባት ላሉ ግን መቆም፡፡ |

| ተ.ቁ | የእግረኛ ማስተላለፊያ የትራፊክ መብራቶች ቀለማትና ህጋቸው | |
|---|---|---|
| | የመብራት ቀለም | ህግ |
| 1 | ቀይ | ለእግረኛ በተከለለ ቦታ መቆም፡፡ |
| 2 | አረንጓዴ | እግረኛ በፍጥነት መንገዱን ማቋረጥ፡፡ |

| ተ.ቁ | ከመንገድ ላይ የትራፊክ ደህንነት ጋር የተያያዙ የትራፊክ ምልክቶች ለምሳሌ የቀረቡ | |
|---|---|---|
| | የትራፊክ ምልክቶች | ትርጉም |
| 1 |  | ቆመህ ቅድሚያ ስጥ:: |
| 2 |  | መኪና ማቆሚያ መኖሩን ይገልፃል:: |
| 3 |  | ለረጅም ሰዓት ማቆም ክልክል ነው:: |
| 4 |  | የምልክቱ መጨረሻ ድረስ ማቆም ክክክል ነው:: |
| 5 |  | ምልክቱ በሚታይበት በኩል ማለፍ ክክክል ነው:: |
| 6 |  | ለእግረኛ የተከለከለ:: |
| 7 |  | ለእግረኛብቻ እንዲሄድ ይፈቅዳል:: |
| 8 |  | የእግረኛ ማቋረጫ:: |
| 9 |  | ተማሪዎች የሚበዙበት ቦታ ስለሆነ ፍትነትን በመቀነስ ተተንቅቆ መንዳት/ማሽከርከር:: |
| 10 |  | አደባባይ ስለሚያጋጥም ተጠንቅቆ መንዳት/ ማሽከርከር:: |
| 11 |  | የትራፊክ ማስተላለፊያ መብራት ስለሚያጋጥም ተጠንቅቆ ማሽከርከር:: |
| 12 |  | መስቀለኛ መንገድ ስለሚያጋጥም ተጠንቅቆ ማሽከርከር:: |

| የትራፊክ ሕግ አስፈላጊነት |
| --- |
| » የመንገድ ላይ ሥነሥርዓት ምልክቶችንና ትዕዛዞችን ለማክበር፡፡ |
| » ለትራፊክ መብራት ትዕዛዝ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት፡፡ |
| » የፍጥነት ወሰን ገደብን ለማክበር፡፡ |
| » በእንቅስቃሴና በማቆም ሂደት ተገቢውን ምልክት በተገቢው ቦታና ጊዜ ለመጠቀም፡፡ |
| » በጥንቃቄ ለማሽከርከር፡፡ |
| » ፍጥነትን ጠብቆ ለማሽከርከር፡፡ |
| » ለእንቅስቃሴ ሕግጋት ተገዥ ለመሆን፡፡ |
| » በተሽከርካሪ የሚደርስ አደጋን ለመቀነስ፡፡ |
| » የአሽከርካሪዎችን መልካም ሥነምግባር ለማጠናከር፡፡ |
| » ከሌሎች መንገድ ተጠቃሚዎች ጋር መንፈሳዊ ትስስር ለመፍጠር፡፡ |

*መመህር/ት፡-* የትራፊክ ሕግን ካለመጠበቅ የሚመጡ ችግሮች በተመለከተ ተማሪዎቹን በኢምቋ ያወያዩ፡፡

**ገላጭ ቃል፡-** ገላጭ ቃል የምንለው የአንድን ነገር ምንነት፣ ባሕሪይ ቀለም አኳኋን፣ የበለጠ ግልፅ እንዲሆንና እንዲታወቅ የሚደርግ ቃል ወይም ሐረግ ነው፡፡ ግላጭን ከአገልግሎት አንፃር ስናየው በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም የስም ገላጭና የግስ ገላጭ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ምሳሌ፡-

(ትልቅ ቤት፣ጎበዝ ተማሪ፣ ረጅም ዛፍ፣ቀጭን ገመድ)

*መርጃ መሣሪያ፡-*

ፎቶዎች/ምስሎች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች/ቻርቶች/ሰንጠረዦች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች የኢምቋ መዝገበ-ምልክት

ግምገማ

- ስለትራፊክ ህግ አስፈላጊነት በኢምቋ መግለፅ መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- የተለያዩ የመንገድ ትራፊክ ህጎችን የሚሳዩ ስእሎችን በመመልከት በኢምቋ መግለፅ መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
- መሠረታዊ የትራፊክ ህጎችን መረዳት መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
- ስለ ትራፊክ ህጎች መጠበቅ አስፈላጊነት በኢምቋ ሀሳብ መስጠት መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- የእግር ጉዞ ሲደረግ ግራን ይዞ ስለመሄድ በኢምቋ መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በቆመ መኪና ተከልለው መንገድ መሻገር እንደሌለባቸው ግንዛቤ መውሰዳቸውን ይገምግሙ፡፡
- በመኪና መንገድ ላይ መጫወት አደገኛ ስለመሆኑ በኢምቋ ማብራራት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የዜብራ ማቋረጫዎችን በመጠቀም መንገድን ስለመሻገር በኢምቋ መናገር መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ በአግባቡ ማሳየት መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
- በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልእክቶችን በኢምቋ ማብራራት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡

## የምዕራፍ አራት መልመጃዎች መልስ

## ትምህርት ሁለት

### ክፍል አንድ

### መልመጃ ሁለት

1. ሠ
2. ሀ
3. ሐ

4. ሰ
5. መ

# ትምህርት አምስት

## ክፍል ሁለት

### መልመጃ አንድ

1. ሐሰት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. እውነት

# ምዕራፍ አምስት

# የዱር እንስሳት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- የዱር እንስሳትን የአኗኗርና የአመጋገብ ሁኔታ በኢምቁ ይገልፃሉ።
- የዱር እንስሳትን ጥቅም በኢምቁ ያስረዳሉ።
- የዱር እንስሳትን ልዩ የባህርይ መግለጫ በኢምቁ ይናገራሉ።
- ለዱር እንስሳት መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ በኢምቁ ይዘረዝራሉ።
- የደን ጭፍጨፋ ለዱር አራዊቶች መሰደድ ምክንያት እንደሚሆን በኢምቁ ያስረዳሉ።
- የተለያዩ የዱር እንስሳት ስሞችን በኢምቁ ይገልፃሉ።
- የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቁ ይሰራሉ።

## ይዘት

- ◊ የዱር እንሰሳት አኗኗርና አመጋገብ
- ◊ የዱር እንሰሳትና የምልክት ስሞቻቸው
- ◊ የዱር እንስሳት ልዩ ባህሪያት
- ◊ የደን ጭፍጨፋና የዱር አራዊቶች
- ◊ ዓረፍተ ነገሮችን መስራት
- ◊ የስም ገላጮች አጠቃቀም
- ◊ የዱር እንስሳትን ልዩ ባህሪያት
- ◊ የደን ጭፍጨፋና የዱር አራዊቶች

## የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 9

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት፣ ትምህርቱን ከመጀመርዎ በፊት ማነቃቂያ እንዲሆን ተማሪዎች ስለሚውቋቸው የዱር እንስሳት መሪ/መነሻ ጥያቄ በኢምቋ በመጠየቅ ይጀምሩ:: ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ:: ከርዕሱ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶችንና ፅንሰ ሀሳቦችን ያስተዋውቁ:: የዱር እንስሳት ስሞችን፣ የአመጋገብና የአኗኗር ሁኔታ በኢምቋ ያስተዋውቁ::

በምዕራፉ ውስጥ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን ተግባሮች፣ ዕይታዊ ንባብን የሚያጎለብቱ ስዕላዊ መግለጫዎችንና ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ እንዲሰሩ ያድርጉ::

በተማሪው መጽሐፍ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ አውራሪስ የሚያወሳውን ምንባብ በዝግታ በኢምቋ በማንበብ ተማሪዎች በትኩረትና በማስተዋል መከታተላቸውን ይቆጣጠሩ:: ተማሪዎችንም በቡድን በመከፋፈል ምንባቡን በድጋሚ እንዲያነቡ ያድርጉ:: ምንባቡንም ምን ያህል እንደተረዱ ይጠይቋቸው::

ምንባቡን መሠረት በማድረግ፣ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን መልመጃዎች እንደመመሪያቸው ሁኔታ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ያሠሯቸው:: ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጡዋቸው::

ምንባቡን ተራ በተራ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲያነቡ በማድረግ የተረዱትን ሐሳብ በራሳቸው ቋንቋና የአገላለፅ ስሜት በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ:: ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው::

የዱር እንስሳትን በመለየት መግለጫቸውን በኢምቋ ያስረዱ:: የዱር እንስሳትን የአመጋገብ ሁኔታና ልዩ ባህሪ ተማሪዎች በኢምቋ እንዲያስረዱ ያለማምዱ:: ለውይይት የሚጋብዝ ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲወያዩ ያመቻቹ:: የተለያዩ የዱር እንስሳትን የስም ገላጮችን በመጠቀም

አኗኗራቸውንና ልዩ ባህሪያቸውን በኢምቋ ዐረፍተ ነገር ይግለፁ፡፡

ተማሪዎች ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁ ያበረታቷቸው፡፡ በክፍለ ጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ የቁልፍ ምልክቶችን አቻ ቃሎቻቸውን በሰሌዳው ላይ በመጻፍና በኢምቋ በማሳየት ማጠቃለያ ክለሳ ያድርጉላቸው፡፡

## ማሳሳቢያ፡-

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም የሐሳብ ልውውጥ ለማከናወን በኢምቋ ይጠቀሙ፡፡

## ቁልፍ ምልክቶች፡-

ሀ) **የዱር እንስሳት፡-** ዱር፣ ቀበሮ፣ ተኩላ፣ ጅብ፣ አውራሪስ፣ ጎሽ፣ ጉማሬ፣ ዝንጀሮ፣ ጦጣ፣ ጉሬዛ፣ ዋልያ፣ ሚዳቋ፣ ዘንዶ፣

ለ) አመጋገብና አኗኗር፡- አመጋገብ፣ ስጋበል፣ ሳርበል፣ አኗኗር፣

## ማብራሪያ፡-

የዱር እንስሳት በየብስ፣ በውሃ ውስጥ፣ በዛፍ ሊይ የሚኖሩ፣ በአየር ላይ የሚበሩና ለማዳ ያልሆኑ እንስሳት ሁለ የዱር እንስሳት ይባላሉ፡፡

የዱር እንስሳት በአፈጣጠራቸው፣ በአኗኗራቸው፣ በአመጋገባቸው፣ በመልክ እና ቅርጻቸው፣ እንዲህ በመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ የተለያዩ ናቸው:: የዱር እንስሳት ሰው ከሚኖርበት አካባቢ ርቀው በአኗኗራቸው በጉድጓድ ወይም ዋሻ ውስጥ፣ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ፣ ረጃጅም ሣር በበዛበት አካባቢ፣ ሣራማ እና ሜዳ በሆነ ቦታ፣ ግራራማ ዛፎች በበዙበት ሥፍራ፣ በሞቃታማ (በበረሃ)፣ ውሃ ባለበት አካባቢ ወይም ውሃ ውስጥ ባሉ ቦታዎች ላይ ይኖራሉ፡፡

አኗኗራቸው እንደ ተፈጥሯቸው ይለያያል:: በአመጋገባቸውም እንደ ተፈጥሯቸው ሣር፣ ቁጥቋጦ እና ቅጠላ ቅጠል የሚበሉ፣ ሥጋ ተመጋቢዎች፣ ትላትል እና ትናንሽ ፍጥረታትን የሚመገቡ፣ ቆሻሻ እና የሞቱ እንስሳትን የሚበሉ፣ አድነው የሚያጠቁ ናቸው:: የአካል ቅርጻቸው እና መልካቸውም እንደየ ዝርያቸው ይለያያል፡፡ በኢትዮጵያ የሚገኙ ዋና ዋና የዱር እንሰሳት የምንላቸው ጅብ፣ ቀበሮ፣ ቀጭኔ፣ የሜዳ አህያ ፣አንበሳ፣ ነብር፣ ጉሬዛ፣ ጦጣ፣ ጉማሬ ወዘተ እና የተለያዩ አእዋፍ ናቸው፡፡

*የዱር እንስሳት ጥቅምና ክብካቤ*

| የዱር እንስሳት ጥቅም | ለዱር እንስሳት መደረግ የሚገባው ክብካቤ |
|---|---|
| • ለቱሪስት መስህብ<br>• የገቢ ምንጭ<br>• ቆዳቸው ለተለያዩ አልባሳትና ጫማ ለማዘጋጀት<br>• ስጋቸው ለምግብነት<br>• ቀንዳቸውና ጥርሳቸው ለጌጣጌጥ መስሪያ | • ህጋዊ ያልሆነ አደንን መከላከል<br>• ደኖችን መንከባከብ<br>• ፓርኮችን ማደራጀት<br>• ሐይቆችንና ባህሮችን መንከባከብ<br>• የደን ጭፍጨፋን መከላከል |

መምህር/ት፡- ለዱር እንስሳት ክብካቤ ካለማድረግ የሚመጡ ችግሮች ላይ በተመለከተ ተማሪዎች በኢምቋ በመጠያየቅ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

## መርጃ መሣሪያ

ፎቶዎች/ምስሎች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች/ሰንጠረዦች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ የኢምቋ መዝገበ-ምልክት

## ግምገማ

* በዱር እንስሳት አመጋገብ ዙሪያ በኢምቋ ውይይት ማድረጋቸውን ያረጋግጡ፡፡
* የዱር እንስሳትን የአኗኗር ሁኔታ ማብረራት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
* የዱር እንስሳትን ልዩ ባህሪያት መግለፅ መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
* የዱር እንስሳትን ጥቅም በኢምቋ ማስረዳት መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
* ዐረፍተ ነገሮችን በመስራት ማሳየት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
* የዱር እንሰሳትን ስም በኢምቋ በትክክል መጥራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
* የዱር እንሰሳትን የሚያሳይ ሥዕልን ከምልክት ስማቸው ጋር ማዛመዳቸውን ይመልከቱ፡፡
* በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልእክቶችን በኢምቋ ማብራራት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
* የዱር እንስሳት በአኗኗራቸው እንደሚለያዩ ለይተው ማወቃቸውን ይገምግሙ፡፡
* ደን ጭፍጨፋ ለዱር አራዊቶች መሰደድ ምክንያት መሆኑን ማስረዳት መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡

* የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ መስራት መቻላቸውን ይገምግሙ።

## የምዕራፍ አምስት መልመጃዎች መልስ

### ትምህርት ሁለት

#### መልመጃ አንድ

1. ሐሰት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. ሐሰት

#### መልመጃ ሶስት

1. እውነት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. እውነት
6. እውነት
7. ሐሰት
8. እውነት
9. ሐሰት
10. ሐሰት

## መልመጃ አራት

1. ሐ
2. ሐ
3. ሀ
4. መ
5. ለ

## መልመጃ ስድስት

1. ሐ
2. ረ
3. ሀ
4. ለ
5. መ

# ምዕራፍ ስድስት

# ባህል

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- የባህልን ምንነት በኢምቁ ያስረዳሉ፡፡
- የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ባህሎች በኢምቁ ያብራራሉ፡፡
- አዎንታዊ ባህሎችን ከአሉታዊ ይለያሉ፡፡
- የአካባቢውን አዎንታዊ ባህሎች ለማዳበር ይሞክራሉ፡፡
- መስማት የተሳናቸውን ባህል አስመልክቶ ልምድ ይለዋወጣሉ፡፡
- አዎንታዊና አሉታዊ  ሐሳብን የያዙ ዐረፍተ ነገሮችን በኢምቁ ይናገራሉ፡፡
- የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቁ ይሰራሉ፡፡

## ይዘት

- የባህል ምንነትና ባህላዊ እምነቶች
- ባህልን የሚያመለክቱ ምልክቶች፣ ስሞች፣ ገላጮችና ግሶች
- የቃላት አገባባዊ ፍቺ
- ባህላችንን እንዴት መጠበቅ አለብን
- የባህሎች አገላለጽና አጠባበቅ
- አዎንታዊ ባህሎችን ከአሉታዊ መለየት
- አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች

## የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 8

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት፣ የእለቱን ትምህርት ከመጀመርዎ በፊት ማነቃቂያ እንዲሆን መሪ/መነሻ ጥያቄ በኢምቋ ይጠይቁ፡፡ ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ፡፡ ከርዕሱ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶችንና ፅንሰ ሀሳቦችን ያስተዋውቁ፡፡ ከባህሎች ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ፣ ስለባህል ምንነትና እንዲሁም የመስማት የተሳናቸው ባህል ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ማብራሪያ ይስጡ፡፡

በምዕራፉ ውስጥ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን ተግባሮች፣ ዕይታዊ ንባብን የሚያጎለብቱ ስዕላዊ መግለጫዎችንና ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

በተማሪው መጽሐፍ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ባህል የሚያወሳውን አጭር ምንባብና ስለ ባህል የተጻፈውን "ሀገሬ ኩራቴ" የሚለውን ሥነ ግጥም በዝግታና ማራኪ በሆነ መልኩ በኢምቋ በማንበብ ተማሪዎች በትኩረትና በማስተዋል መከታተላቸውን ይቆጣጠሩ፡፡ ተማሪዎችንም በቡድን በመከፋፈል ምንባቡን በድጋሚ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ምንባቡንም ምን ያህል እንደተረዱ ይጠይቋቸው፡፡

ምንባቡን መሠረት በማድረግ፣ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን መልመጃዎች እንደመመሪያቸው ሁኔታ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ያሠሯቸው፡፡ ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው፡፡

ምንባቡን ተራ በተራ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲያነቡ በማድረግ የተረዱትን ሐሳብ በራሳቸው ቋንቋና የአገላለፅ ስሜት በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው፡፡

የሀገራችንን የተለያዩ ባህሎች ባህሪያት የሚያሳዩ የተለያዩ ሥዕሎችን እንዲያዩና ያዩትን በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡ በጥንድና በቡድን ሆነው ስለ ጠቃሚና ጎጂ ባህሎች የሚያውቁትን ያህል ባህል በጠቀሜታውና በጉዳቱ ላይ እንዲከራከሩ ያድርጉ፡፡ በጥንድና በቡድን ሆነው ስለሚወዱት የባህል ዓይነት ንግግር እንዲያደርጉ ያመቻቹ፡፡ ለውይይት የሚጋብዝ ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ ሆነው በኢምቋ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በጥያቄዎቹ ላይ የተመሠረቱ አስፈላጊ ትምህርቶችን ይስጡ፡፡ ተማሪዎች ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁ ያበረታቱ፡፡ በክፍለ ጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ ቁልፍ

ምልክቶችን አቻ ቃሎቻቸውን በሰሌዳው በመጻፍ በኢምቋ በማሳየት ማጠቃለያ ክለሳ ያድርጉ።

## ማሳሳቢያ፡-

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም የሐሳብ ልውውጥ ለማከናወን በኢምቋ ይጠቀሙ።

## ቁልፍ ምልክቶች፡-

ባህል፣ ባህላዊ፣ ጎጂ፣ ጠቃሚ፣ ባህላዊ አልባሳት፣ ባህላዊ ምግቦች፣ ባህላዊ ጭፈራዎች፣ ባህላዊ ጋብቻ፣ መረዳዳት፣ መከባበር፣ መቻቻል፣ ሠርግ፣ ሥርዓት፣ ማኅበራዊ ግንኙነት፣ ክብረ በዓል፣ ደጋ (ተራራማ አካባቢ)፣ ቆላ (ረባዳማ አካባቢ)፣ ምርቃት፣ ዕድር፣ ዕቁብ

## ማብራሪያ፡-

ባህል የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና የባህል ድርጊቶች (ዩኔስኮ) እ.ኤ.አ በ1982 ዓ.ም ሜክሲኮ ላይ ባደረገው ስብሰባ ላይ ባህልን አስመልክቶ የተደረሰበት ድንጋጌ እንዲህ ይላል።

“ባህል ሰው ልጅ ሰብዓዊና ምክንያታዊ ፍጡር እንዲሆን ያስቻሉት ወይንም ከሌሎች ፍጡራን ለመለየት ያበቁትን መሠረታዊ ጉዳዮች የያዘ ፅንሰ ሐሳብ ነው። አንድ ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ ተለይቶ የሚታወቅበት የአኗኗር ዘይቤዎቹ፣ ዕምነቶቹ፣ ትውፊቶቹ፣ በአጠቃላይ ቁሳዊና ሕሊናዊ ሀብቶቹ የሚጠቃለሉት በባህል ስር ነው”።

ባህል ከትውልድ ትውልድ ከአባቶቻችን የምንወርሰው ወግና ሥርዓት ሲሆን፣ የአንድ ሀገር ሀብት፣ ልዩ የማንነት መገለጫ፣ ኅብረ ቀለም፣ የኅብኝዎች መስህብ፣ ውበትና ድንቅ የሆነ ጸጋ ነው። የአንድ ሀገር አለባበስ፣ የምግብ አዘገጃጀት፣ የዓውደ ዓመት አከባበር፣ የጭፈራ ዓይነቶች ለባህል መመስረት መነሻዎች ሲሆኑ አንድ ማኅበረሰብ ከሌላው የሚለይበትን የማንነት አሻራ ይፈጥሩለታል። ለምሳሌ ደጋማ አካባቢ የሚኖር ሕዝብ ቆላማ አካባቢ ከሚኖር ሕዝብ በባህሉና በአኗኗር ሥልቱ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የተለየ ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከምድር ወገብ በስተሰሜን፣ በአፍሪካ ምሥራቃዊ ክፍል የምትገኝ ናት። ብቸኛም ባለ 13 ወር የሆነች አገር ናት። እንደ ብሔር ብሄረሰቦቿ ብዛት በቋንቋ፣ በአለባበስ፣ በማኅበራዊ ግንኙነት፣ በሠርግና በለቅሶ ሥርዓቶች፣ በእርቅ አፈጻጸም፣ በሕክምና፣ በቤት አሠራር፣ በምግብ ዝግጅት፣ በአመጋገብና በመሳሰሉት ሁሉ እጅግ በርከት ያሉ ባህላዊ ቅርሶች ያሏት ሀገር ናት።

| የባህል ዓይነቶች | |
|---|---|
| ሠርግ<br>ማኅበራዊ ግንኙነት<br>እርቅ<br>የመኖሪያ ቤት<br>አሠራር<br>ምግብ ዝግጅት<br>በአመጋገብ | በእጅ ሥራ<br>በክብረ በዓል አከባበር<br>በሙዚቃ መሣሪያ<br>አለባበስ |

መምህር/ት፡- ከላይ የቀረቡትን ባህልና የባህል ዓይነቶችን መነሻ በማድረግ ስለ ተለያዩ ብሔሮች/ ብሔረሰቦች ተማሪዎች በኢምቋ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

| ጠቃሚ ባህል | ጎጂ ባህል |
|---|---|
| ማኅበር | ያለ ዕድሜ ጋብቻ |
| ዕድር | ጠለፋ |
| እቁብ | ጥንቆላ |
| መረዳዳት | አስገድዶ መድፈር |
| ባህላዊ አልባሳት | ሱስ አስያዥ ዕፆችን መጠቀም |
| ደቦ | ለውበትና ለእምነት ሲባል አካልን በስለት መተልተል |

መምህር/ት፡- ከላይ የቀረቡትን ጠቃሚና ጎጂ የባህል ዓይነቶችን መነሻ በማድረግ ተማሪዎች በኢምቋ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

| የሀገራችን መለያ የሆኑ ምግብ፣ መጠጥና ቅመማ ቅመም | | |
|---|---|---|
| ምግብ | መጠጥ | ቅመማ ቅመም |
| እንጀራ | ጠላ | በርበሬ |
| ድፎ ዳቦ | ጠጅ | ሽሮ |
| ክትፎ | ብርዝ | ሚጥሚጣ |
| ቆጮ | አረቄ | እርድ |
| ሽሮ ወጥ | ሻሜታ | ድልህ |
| ዶሮ ወጥ | ቀሪቦ | |

መምህር/ት፡- በሀገራችን የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች መለያ የሆኑ የምግብ ዓይነቶች ላይ ተማሪዎችን በኢምቋ ያወያዩ፡፡

## መርጃ መሣሪያ

ፎቶዎች/ምስሎች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች/ሰንጠረዦች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ የኢምቋ መዝገበ-ምልክት

## ግምገማ

- የባህልን ምንነት በኢምቋ ማስረዳት መቻላቸውን ይገምግሙ::
- ስለ አካባቢያቸው ባህል በኢምቋ መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ::
- ስለአዎንታዊ ባህል ያላቸውን አስተያየትና ምክንያት በኢምቋ ማስረዳት መቻላቸውን ያረጋግጡ::
- ስለአሉታዊ ባህል ያላቸውን አስተያየትና ስሜት በኢምቋ መግለፅ መቻላቸውን ያረጋግጡ::
- በአካባቢያቸው ያለውን የመስማት የተሳናቸውን ባህል በምሳሌና በድራማ መልክ ለማሳየት መሞከራቸውን ይከታተሉ::
- አዎንታዊ ባህሎችን ከአሉታዊ መለያታቸውን ያረጋግጡ::
- በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልእክቶችን በኢምቋ ማብራራት መቻላቸውን ይከታተሉ::
- አሉታዊና አዎንታዊ ዐረፍተ ነገሮች በኢምቋ መናገር መቻላቸውን ያረጋግጡ::
- የቁልፍ ምልክቶች እሴቶችን ማብረራት መቻላቸውን ያረጋግጡ::
- የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ ባህሎች የሚያሳይ ሥዕልን በኢምቋ መግለፅ መቻላቸውን ይመልከቱ::

## የምዕራፍ ስድስት መልመጃዎች መልስ

## ትምህርት ሁለት

### መልመጃ አንድ

1. እውነት
2. ሐሰት

3. ሐሰት
4. እውነት
5. እውነት
6. ሐሰት
7. ሐሰት
8. ሐሰት
9. ሐሰት

## መልመጃ ሁለት

1. ባህል
2. ወግ እና ሥርዓት
3. ደጋማና ቆላማ
4. መከባበርና መቻቻል
5. 13

# ምዕራፍ ሰባት

# ጎጂ ልማዶች

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኂላ፡

- የጎጂ ልማዶችን ምንነት በኢምቋ ያስረዳሉ፡፡
- በአካባቢያቸው የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዶችን በኢምቋ ያብራራሉ፡፡
- የቁልፍ ምልክቶች እሴቶችን ያብራራሉ፡፡
- ጎጂ ባህሎችን አስመልክቶ አስገዳጅ ዐረፍተ ነገሮችን በኢምቋ ይናገራሉ፡፡
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያመጡትን ጉዳት በዝርዝር በኢምቋ ይገልፃሉ፡፡
- የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ ይሰራሉ፡፡

## ይዘት

- ◊ ጎጂ ልማዶች የሚያመጡት ችግር፣ ጉዳትና ተፅእኖ
- ◊ ጎጂ ልማዶችን የሚያመላክቱ ስሞች፣ ገላጮችና ግሶች
- ◊ በአካባቢያችን ያሉ ጎጂ ልማዶች አገላለጽ
- ◊ ከጎጂ ልማዶች ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶች
- ◊ አዎንታዊና አሉታዊ ሀሳብ የያዙ ዐረፍተ ነገሮች

## የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 12

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት፣ የእለቱን ትምህርት ከመጀመርዎ በፊት ማነቃቂያ እንዲሆን መሪ/መነሻ ጥያቄ በኢምቋ ይጠይቁ:: ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ:: ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶችንና ፅንሰ ሀሳቦችን ያስተዋውቁ::

በምዕራፉ ውስጥ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን ተግባሮች፣ ዕይታዊ ንባብን የሚያጎለብቱ ስዕላዊ መግለጫዎችንና ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ እንዲሰሩ ያድርጉ::

በተማሪው መጽሐፍ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ስለሚያስከትሉት ስነልቦናዊና አካላዊ ጉዳት የሚያወሳውን የሚያወሳውን ምንባብ በዝግታና ትርጉም ሰጪ በሆነ መልኩ በኢምቋ በማንበብ ተማሪዎች በትኩረትና በማስተዋል መከታተላቸውን ይቆጣጠሩ:: ተማሪዎችንም በቡድን በመከፋፈል ምንባቡን በድጋሚ እንዲያነቡ ያድርጉ:: ምንባቡንም ምን ያህል እንደተረዱ ይጠይቋቸው::

ምንባቡን መሠረት በማድረግ፣ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን መልመጃዎች እንደመመሪያቸው ሁኔታ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ያሠሯቸው:: ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው::

ምንባቡን ተራ በተራ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲያነቡ በማድረግ የተረዱትን ሐሳብ በራሳቸው ቋንቋና የአገላለፅ ስሜት በኢምቋ እንዲገልፁና እንዲወያዩ ያድርጉ::ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው:: ተማሪዎችም ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁና እንዲመልሱ ያድርጉ::

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚያሳዩ ሥዕሎች በማሳየት በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ:: ለውይይት የሚጋብዝ ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ ሆነው በኢምቋ እንዲወያዩ ያድርጉ:: በጥያቄዎቹ ላይ የተመሠረቱ አስፈላጊ ትምህርቶችን ይስጡ::

ተማሪዎች ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁ ያበረታቱ:: በክፍለ ጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ ቁልፍ ምልክቶችን አቻ ቃሎቻቸውን በሰሌዳው በመጻፍ በኢምቋ በማሳየት ማጠቃለያ ክለሳ ያድርጉ::

**ማሳሳቢያ፡-**

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም የሐሳብ ልውውጥ ለማከናወን በኢምቋ ይጠቀሙ፡፡

**ቁልፍ ምልክቶች፡-**

ድርጊት፣ ልማድ፣ ችግር፣ እንጥል ማስቆረጥ፣ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ፊት መቧጠጥ፣ ጠለፋ፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ሱስ፣ ዕፆች፣ ግግ ማስቧጠጥ፣ ጥቃት፣ የሴት ልጅ ጥቃት፣ የህፃናት ጥቃት፣ ጎጂ፣ መከራ፣ ሕግ፣ ወንጀል

## ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

**ማብራሪያ፡-**

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚባሉት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ስር ሰደው የተንሰራፉ ጉዳት የሚያስከትሉና የማይጠቅሙ የተግባር ልምምዶች ናቸው፡፡ አንዳንድ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ረጅም ዘመን ስለቆዩ እንደ ባህል ሲቆጠሩ ይታያል፡፡ በተጨማሪም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የእምነት አንድ ክፍል ተደርገው ስለሚቆጠሩ፤ በማህረሰቡ ውስጥ ተደጋግመው በመፈጸም ረጅም ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሙሉ ለሙሉ ባይወገዱም፤ በዚህ ዙሪያ ተከታታይ ትምህርት እየተሰጠ በመሆኑ በርካታ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሱ በመሄድ ላይ ናቸው፡፡

## ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የምንላቸው

ምሳሌ፡- (ያለ እድሜ ጋብቻ፣ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ግግ ማሰቧጠጥ፣ ጠለፋ፣ አስገድዶ መድፈር፣ ሱስ አስያዥ ዕፆችን መጠቀም፤ ለውበትና ለዕምነት ሲባል አካልን በስለት መተልተል)

## ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት የሚያስከትሉው ጉዳት፤

- የአካልና ሥነልቦና ጉዳት ያደርሳል፡፡
- በቤተሰብና በማህረሰብ መካከል ያለውን ጤናማ ግንኙነት ያውካል፡፡
- በግል፣ በቤተሰብ፣ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡
- ለእድገትና ለስልጣኔ እንቅፋት ይሆናል፡፡

| የጎጂ ልማድ ገላጭ ቃሎች | |
|---|---|
| እንጥል ማስቆረጥ | ቀጥቃጭ |
| የሴት ልጅ ግርዛት | አስማት |
| ጠለፋ | ጥንቆላ |
| | የሴት ልጅ ጥቃት |

## ጎጂ ልማዳዊ ድርጊትን ለመከላከል የመፍትሄ ሐሳቦች፤

- ማኅበረሰቡን ማስተማር
- ስለ ጉዳዩ በቂ መረጃን ተደራሽ ማድረግ
- የሕግ ከለላ መስጠት
- የሴቶችን ጥቃት መከላከል
- የህፃናትን ጥቃት መቆጣጠር

መምህር/ት፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያመጡትን ችግሮችንና እነዚህን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ተማሪዎች በኢምቋ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

## የስም ገላጭ ቃላት

የስም ገላጭ ቃላት ከስም በፊት በመገኘት ስምን የበለጠ የሚገልጡ፣ የሚያጎለምሱ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡-

» ዳንኤል በትምህርቱ _ጎበዝ ተማሪ_ ነው፡፡ በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ‹ተማሪ› የሚለው ስም ጎበዝ በሚለው ገላጭ ቃል ስለተገለጠ ዳንኤል በትምህርቱ ጎበዝ ተማሪ እንደሆነ ያስረዳናል፡፡

» _ቀጭኗ ልጅ_ የኛ ክፍል ተማሪ ናት፡፡ ከብዙ ልጆች መካከል ቀጭን የሆነችው በዚህ መልኩ እንድትለይና የበለጠ እንድትገለጥ ሆኗል፡፡

» ስለዚህ *ጎበዝ* እና *ቀጭኗ* የሚሉት ቃላት ስሞችን በመግለጣቸው ምክንያት <u>የስም</u> ገላጮች ተብለው ይጠራሉ፡፡

## መርጃ መሣሪያ

ፎቶዎች/ምስሎች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች/ሰንጠረዦች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ የኢምቋ መዝገበ-ምልክት

## ግምገማ

* በአካባቢያቸው ስለሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በኢምቋ ማብረራት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
* ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያመጡትን ጉዳት በዝርዝር በኢምቋ መግለፅ መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
* ስለ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሁኔታ በድራማ መልክ በአግባቡ በኢምቋ ማሳየት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
* የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ መስራት መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
* በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልእክቶችን በኢምቋ ማብራራት  መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
* ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚባሉት ምን ምን እንደሆኑ በኢምቋ መተንተን መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

## የምዕራፍ  ሰባት መልመጃዎች መልስ

# ትምህርት ሁለት

## ክፍል አንድ

### መልመጃ አንድ

1. 14
2. 5
3. በየበረንዳው እና መንገድ ዳር
4. ሦስተኛ ክፍል
5. በሦስት

## መልመጃ ሁለት

1. ለ
2. መ
3. ሐ
4. ሀ
5. መ

# ምዕራፍ ስምንት

# ባህላዊ ጨዋታዎች

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- በየአካባቢያቸው የሚዘወተሩ ባህላዊ ጨዋታዎችን በኢምቋ ያስረዳሉ፡፡
- የባህላዊ ጨዋታዎችን ባህሪያት በኢምቋ ያብራራሉ፡፡
- ምልክቶችንና ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ባህላዊ ጨዋታዎችን በኢምቋ ይገልፃሉ፡፡
- ከባህላዊ ጨዋታዎች ጋር የተያያዙ ምልክቶችን ይጠቀማሉ፡፡
- የተለያዩ የስምና የግስ ገላጮችን ይጠቀማሉ፡፡
- የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ ይሰራሉ፡፡

## ይዘት

- ◊ ባህላዊ ጨዋታዎች
- ◊ በአካባቢያችን የሚዘወተሩ ባህላዊ ጨዋታዎችና የመጫወቻ መሳሪዎች
- ◊ ባህላዊ ጨዋታዎችን የሚገልፁ ስሞች፣ የፊት መግለጫና ምልክቶች
- ◊ የባህላዊ ጨዋታዎች አገላለጽና የጨዋታ ህጎች
- ◊ የቃላት አገባባዊ ፍቺ
- ◊ የስምና የግስ ገላጮችን የያዙ ዓረፍተ ነገሮች

## የተመደበው ክፍለ ጊዜ፦ 8

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት፣ ትምህርቱን ከመጀመርዎ በፊት ማነቃቂያ እንዲሆን መሪ/መነሻ ጥያቄ በኢምቋ ይጠይቁ:: ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ:: ከርዕሱ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ምልክቶችንና ፅንሰ ሀሳቦችን ያስተዋውቁ::

በምዕራፉ ውስጥ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን ተግባሮች፣ ዕይታዊ ንባብን የሚያጎለብቱ ስዕላዊ መግለጫዎችንና ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ እንዲሰሩ ያድርጉ::

በተማሪው መጽሐፍ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ባህላዊ ጨዋታዎች የሚያወሳውን ምንባብ በዝግታና ትርጉም ሰጪ በሆነ መልኩ በኢምቋ በማንበብ ተማሪዎች በትኩረትና በማስተዋል መከታተላቸውን ይቆጣጠሩ:: ተማሪዎችንም በቡድን በመከፋፈል ምንባቡን በድጋሚ እንዲያነቡ ያድርጉ:: ምንባቡንም ምን ያህል እንደተረዱ ይጠይቋቸው::

ምንባቡን መሠረት በማድረግ፣ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን መልመጃዎች እንደመመሪያቸው ሁኔታ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ያሠሯቸው:: ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው::

ምንባቡን ተራ በተራ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲያነቡ በማድረግ የተረዱትን ሐሳብ በራሳቸው ቋንቋና የአገላለፅ ስሜት በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ:: ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው:: ተማሪዎችም ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁና እንዲመልሱና እንዲወያዩ ያድርጉ::

ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎችን የሚወደቱን/የሚችሉትን ባህላዊ ጨዋታ በክፍሉ ውስጥ እንዲሳዩ ይጋብዙ:: የባህላዊ ጨዋታዎችና ባህሪያቸው አጭር ማብራሪያ በመስጠት ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ:: ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚዘወተሩና የሚያውቁትን ባህላዊ ጨዋታ ባህሪይና አጨዋወት እንዲገልፁ ያድርጉ::

ተማሪዎች ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁ ያበረታቱ:: የጣት ፊደላትን በማንበብ አቻ ምልክቶቻቸውን

እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡ በክፍለ ጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ ቁልፍ ምልክቶችን አቻ ቃሎቻቸውን በሰሌዳው በመጻፍ በጣት ፊደላትና በኢምቁ በማሳየት ማጠቃለያ ክለሳ ያድርጉ፡፡

## ማሳሳቢያ፡-

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም የሐሳብ ልውውጥ ለማከናወን በኢምቁ ይጠቀሙ፡፡

## ቁልፍ ምልክቶች፡-

የገና ጨዋታ፣ ባህላዊ፣ ፈረስ ግልቢያ፣ ቅልልቦሽ፣ ገመድ ጉተታ፣ ገበጣ፣ ዕቃ ዕቃ ጨዋታ፣ መሐረቤን ያያችሁ፣ ገመድ ዝላይ

## ማብራሪያ፡-

### ባህላዊ ጨዋታዎች

ሰዎች እንደሚኖሩበት አካባቢ፣ ማኅበረሰብ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ልምድ የተለያዩ የባህላዊ ጨዋታዎች ሊኖሯቸው ይችላል፡፡ እነዚህ ጨዋታዎችም ሰዎች እንደ ዕድሜያቸው መጠንና እንደየፆታቸው ልዩነት በነጠላና በቡድን ሆነው ይጫወቷቸዋል፡፡

ባህላዊ ጨዋታዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን፣ ለሰው ልጆች የተለያዩ ጠቀሜታዎችን ይሰጣሉ፡፡ ማኅበራዊ ግንኙነትን ያዳብራሉ፣ በራስ መተማመንንና የተሳታፊነትን ሥነልቦና ያበለጽጋሉ፤ የአካል ወይም የጡንቻ ጥንካሬን ያስገኛሉ፡፡

ልጆች እንደ አካባቢያቸው፣ እንደ ቋንቋቸው፣ እንደ ጾታቸውና ሃይማኖታቸው ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ገበጣ፣ ቅልልቦሽ፣ ሰኞ ማክሰኞ፣ ገመድ ጀዝላይ፣ ሌባ እና ፖሊስ፣ ተሸክሞ መውሰድ፣ ዕቃ ዕቃ ጨዋታ፣ መሀረቤን ያያችሁ፣ አኩኩሉ፣ ድብብቆሽ፣ የመሳሰሉትን ጨዋታዎች በቡድን ወይም በነጠላ በመሆን ይጫወታሉ፡፡

| ባህላዊ ጨዋታዎች | |
|---|---|
| መሐረቤን ያያችሁ | ገበጣ |
| ድብብቆሽ | ጠጠር |
| ገመድ ዝላይ | ቅልልቦሽ |
| ሌባ እና ፖሊስ | ዕቃ ዕቃ ጨዋታ |
| የገና ጨዋታ | |

## የባህላዊ ጨዋታዎች ጠቀሜታዋች

- ግንኙነትን ለማዳበር
- በራስ መተማመንን
- የተሳታፊነትን ስነ ልቦና ለማበልፀግ
- ለሰውነት ጥንካሬ
- ለጡንቻ ጥንካሬ
- ለመዝናናት

መምህር/ት፡- ባህላዊ ጨዋታዎችንና ጠቀሜታቸውን በተመለከተ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል በኢምቋ በመጠያየቅ እንዲወያ ያድርጉ፡፡

### መርጃ መሣሪያ፡-

ፎቶዎች/ምስሎች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች፣ ቻርቶች/ሰንጠረዥች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ የኢምቋ መዝገበ-ምልክት

### ግምገማ

- ስለሚያውቁት ባህላዊ ጨዋታና አጨዋወት በኢምቋ ገለፃ ማድረግ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የተለያዩ የስምና የግስ ገላጮችን በመጠቀም ዐረፍተ ነገሮችን በኢምቋ መገንባት መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡
- በአካባቢያቸው ስለሚዘወተሩ ባህላዊ ጨዋታዎች በኢምቋ ማስረዳት መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- የባህላዊ ጨዋታዎችን ባህሪያት በተገቢው ሁኔታ በኢምቋ ማብራራት መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልእክቶችን በኢምቋ ማብራራት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ መስራት መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
- በጣት ፊደላት የሚቀርቡ ቃሎችን አቻ ምልክት በአግባቡ በኢምቋ ማሳየት

መቻላቸውን ይከታተሉ።

## የምዕራፍ ስምንት መልመጃዎች መልስ

## ትምህርት ሁለት

### ክፍል ሁለት

### መልመጃ አንድ

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. እውነት
6. እውነት

### መልመጃ ሶስት

1. ሴቶችም ወንዶችም
2. መጠነኛ ኳስና ቆርኪ
3. ደርዳሪ
4. በኳሷ አፍርሶ
5. ደርዳሪዎችን ለመምታት
6. ማነጣጠር
7. ቅልጥፍና
8. የሚወደድ
9. የመሸወድ
10. እንዲያምር

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ተረት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ከተረት የሚገኙ ጥቅሞችን በኢምቋ ያስረዳሉ፡፡
- ትምህርት ሰጪ ተረቶችን በኢምቋ ይተርታሉ፡፡
- የሚያውቁትን ተረት በኢምቋ ያሳያሉ፡፡
- ስለ ስነ-ቃል ዓይነቶች በኢምቋ ይወያያሉ፡፡
- ስለተረት አስፈላጊነት በኢምቋ ይነጋገራሉ፡፡
- ተመሳሳይ ምልክቶችን ከቃላት ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ ይሰራሉ፡፡

## ይዘት

- ◊ የተረት ምንነትና ጥቅም
- ◊ ስምና ቅፅል የያዙ ዓረፍተ ነገሮች
- ◊ በአካባቢያችን የሚዘወተሩ ተረቶች
- ◊ የተረቶች አገላለጽና አጠቃቀም
- ◊ የስነ-ቃል ዓይነቶች
- ◊ ተረትን የሚያመላክቱ ስሞችና አገላለፆች
- ◊ ገላጮችንና ግሶችን የሚያመለክቱ ምልክቶች

## የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 9

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት፣ የእለቱን ትምህርት ከመጀመርዎ በፊት ማነቃቂያ እንዲሆን መሪ/መነሻ ጥያቄ በኢምቋ ይጠይቁ። ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ። ስለ ተረት ምንነትና ስለ ተረት አወራር እንዲሁም ተረትን የሚመለከቱ ቁልፍ ምልክቶችንና ፅንሰ ሀሳቦችን ያስተዋውቁ።

በምዕራፉ ውስጥ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን ተግባሮች፣ ዕይታዊ ንባብን የሚያጎለብቱ ስዕላዊ መግለጫዎችንና ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ እንዲሰሩ ያድርጉ።

በተማሪው መጽሐፍ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተረቱን በዝግታና ትርጉም ሰጪ በሆነ መልኩ በኢምቋ በማንበብ ተማሪዎች በትኩረትና በማስተዋል መከታተላቸውን ይቆጣጠሩ። ተማሪዎችንም በቡድን በመከፋፈል ተረቱን በድጋሚ እንዲያነቡ ያድርጉ። ተረቱንም ምን ያህል እንደተረዱ ይጠይቋቸው።

ምንባቡን መሠረት በማድረግ፣ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን መልመጃዎች እንደመመሪያቸው ሁኔታ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ያሠሯቸው። ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው።

ተረቱን ተራ በተራ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲያነቡ በማድረግ የተረዱትን ሐሳብ በራሳቸው ቋንቋና የአገላለፅ ስሜት በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ። ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጡዋቸው። ተማሪዎችም ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁና እንዲመልሱ ያድርጉ።

የሚያውቁትን ተረት ለክፍሉ በኢምቋ እንዲናገሩና እንዲወያዩ ያድርጉ። ሁለት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም (ምልክት) ሊኖራቸው እንደሚችል ይግለፁ። ለውይይት የሚጋብዝ ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ ሆነው በኢምቋ እንዲወያዩ ያድርጉ። በጥያቄዎቹ ላይ የተመሠረቱ አስፈላጊ ትምህርቶችን ይስጡ።

ተማሪዎች ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁ ያበረታቱ፡፡ በክፍለ ጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ ቁልፍ ምልክቶችን አቻ ቃሎቻቸውን በሰሌዳው በመጻፍ በኢምቋ በማሳየት ማጠቃለያ ክለሳ ያድርጉ፡፡

## ማሳሳቢያ

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም የሐሳብ ልውውጥ ለማከናወን በኢምቋ ይጠቀሙ፡፡

## ቁልፍ ምልክቶች፡-

ተረት፣ ጭብጥ፣ ስነ-ምግባር፣ ዕውቀት፣ ብልሃት፣ ጥበብ፣ ተንኮል፣ ግጥም፣ ስነ ቃል፣ ስንኝ፣ አስቂኝ፣ አሳዛኝ፣ አስደንጋጭ፣ ክፋት፣ ደግነት፣ ቁም ነገር፣ አዝናኝ፣

## ማብራሪያ፡-

ተረት፡- በድሮ ጊዜ ወይም ከዕለታት አንድ ቀን በአንድ ቦታ እገሌና እገሌ የሚባሉ ሁለት ሰዎች ነበሩ፡፡ እንዲህ፣ እንዲህ ያለ ነገር ፈፀሙ፡፡ ከዚያ እንዲህ ሆኑ እዚ ገቡ፡፡ እንዲህ ሆኑ፡፡ በመጨረሻም እንዲህ ያለ ነገር ደረሰባቸው፡፡ እያለ የሚተርክና ወደፊት የሚጓዝ ትረካ ነው፡፡

እንቆቅልሽ፡- በጠያቂና በተጠያቂ መካከል የሚደረግ የልጆችን አዕምሮ ለማስላት አካባቢያቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ የአስተሳሰባቸውን አድማስ ለማስፋት የሰውን የእንስሳትንና የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ባህሪያትና ቅርፅ እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚረዱ የውድድር መንፈስ የሚታይበት የጥያቄና መልስ ስነ ቃል ነው፡፡ ይህ የስነ ቃል ዓይነት የጠያቂውንም ሆነ የተጠየቀውን ችሎታና ማስተዋል በአካባቢ ለሚፈፀሙ ክንዋኔዎች ለተፈጥሮና ለሰው ባህርያት ንቁ መሆንን ይጠይቃል፡፡

ተውኔት፡- የራሱ ባህሪያት ያሉት አንድ የስነ ፅሁፍ ዘርፍ ነው፡፡ ተውኔት የተመረጠን የማህበረሰብ ገፅታ በማሳየት ረገድ ከሌሎች የስነ ፅሁፍ ዘርፎች የሚጋራቸው ኪነ ጥበባዊ ባህሪያት አሉት፡፡ ተውኔት በደራሲው ወይም በፀሐፊ ተውኔቱ በተመረጠ ጠባብ የቦታና የጊዜ ክልል ሕወትን በድረጊት በመድረክ ላይ የሚያቀርብ ነው፡፡

ምሳሌያዊ አነጋገር፡- በማህረሰቡ ልማዳዊ ስምምነት መሠረት የሚፈጠር በቁጥብና በምርጥ ቃላት በአጭሩ የሚነገር የተጨመቀ ጥልቅ ሐሳብን የያዘ የስነ ቃል ዓይነት ነው፡፡

**ስነ ግጥም፡-** የቋንቋ ሰዋሰውን ሳይጠብቅ ለየት ባለ መልኩ በስንኞች ተቀነባብሮ ቤት እመታና እየደፋ የሚቀርብ ፅሑፍ ነው፡፡ ግትም በጥቂቱ ምርጥና ምጥን ቃላት አማካኝነት ከፍተኛ ቁም ነገሮችን ስሜትን ሊነካ በሚችል መልኩ ያቀርባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሙዚቃዊ ቃናው የመሳብና የመማረክ ኃይል ስላለው ለስሜታችን ቅርብ ነው፡፡

**ፈሊጣዊ አነጋገር፡-** ቃላትን ወይም ሐረጎችን በመጠቀም ዱሮ ከነበራቸው ትርጉም ለየት ያለ ትርጉም እንዲሰጡ በማድረግ የምንጠቀምበት የስነ ቃል ዓይነት ነው፡፡

### መርጃ መሣሪያ

ፎቶዎች/ምስሎች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች/ቻርቶች/ሰንጠረዦች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ የኢምቋ መዝገበ-ምልክት

### ግምገማ

- የተረትን አስፈላጊነትና ጥቅም በኢምቋ መግለፅ መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
- ያነበቡትንና  የሚያውቁትን የተረት መልዕክት በራሳቸው መንገድ በኢምቋ መናገር መቻላቸውን ይመልከቱ፡፡
- ተረቶችን በኢምቋ መተረታቸውን ይገምግሙ፡፡
- የክፍል ጓደኞቻቸው ያቀረቡት ተረት ላይ በኢምቋ ውይይት ማድረግ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ዐረፍተ ነገሮች በማሟላት በኢምቋ በአግባቡ ማሳየት መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
- በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልእክቶችን በኢምቋ ማብራራት  መቻላቸውን ይከታተሉ፡፡

# የምዕራፍ ዘጠኝ መልመጃዎች መልስ

## ተረት አንድ

## ትምህርት ሁለት

### መልመጃ አንድ

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. እውነት
6. እውነት
7. ሐሰት
8. እውነት

### መልመጃ ሁለት

1. ሰ
2. ሀ
3. መ
4. ሐ
5. ሀ
6. መ
7. ሰ

## መልመጃ ሶስት

1. የሰባ የፍየል ሙክት
2. ደብተራዎች
3. አረዱት
4. እንጃልህ
5. ደብተራ

### ተረት ሁለት

## መልመጃ ሁለት

1. ስልቻ
2. አደን
3. ፍርድ
4. ጠምዶ
5. ከታፈነ

# ትምህርት ሶስት

## መልመጃ ሁለት

1. ነብሩ
2. አዳኞቹ
3. ገበሬው
4. ገበሬው
5. ነብሩ
6. ገበሬው
7. ነብሩ
8. ገበሬው
9. ጦጣ
10. ጦጣ

# ምዕራፍ አስር

# ተውኔት

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡

- ስለ ተውኔት ጥቅምና አስፈላጊነት በኢምቋ ያስረዳሉ፡፡
- አጫጭር ተውኔቶችን በኢምቋ በመስራት ለክፍል ጓደኞቻቸው ያሳያሉ፡፡
- ምልክቶችንና ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ያዩትን ተውኔት መልዕክቱን በራሳቸው አገላለፅ በኢምቋ ያብራራሉ፡፡
- ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገሮችን በኢምቋ ይመሠርታሉ፡፡
- የጎደሉ ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ ይሰራሉ፡፡

## ይዘት

- ◊ የተውኔት ምንነት፣ አስፈላጊነትና ጥቅም
- ◊ የተውኔት ባህሪያት
- ◊ ተውኔትን የሚያመለክቱ ምልክቶችና የፊት መግለጫዎች
- ◊ የሬዲዮ ድራማ
- ◊ የቴሌቪዥን ድራማ
- ◊ የጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገሮች አመሰራረት

## የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 9

## የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር/ት፣ የእለቱን ትምህርት ከመጀመርዎ በፊት ማነቃቂያ እንዲሆን መሪ/መነሻ ጥያቄ በኢምቋ ይጠይቁ፡፡ ቁልፍ ምልክቶችን ያስተዋውቁ፡፡ ስለ ተውኔት ምንነትና ባህሪያት የሚገልፁ ቁልፍ ምልክቶችንና ፅንሰ ሀሳቦችን ያስተዋውቁ፡፡

በምዕራፉ ውስጥ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን ተግባሮች፣ ዕይታዊ ንባብን የሚያጎለብቱ ስዕላዊ መግለጫዎችንና ለውይይት የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአግባቡ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

በተማሪው መጽሐፍ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ቡድንና የግል ጥናት የቀረበውን ተውኔታዊ ትዕይንት ለተማሪዎች በሚመችና ትርጉም ሰጪ በሆነ መልኩ በኢምቋ በማንበብ ተማሪዎች በትኩረትና በማስተዋል መከታተላቸውን ይቆጣጠሩ፡፡ ተማሪዎችንም በቡድን በመከፋፈል ምንባቡን በድጋሚ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ምንባቡንም ምን ያህል እንደተረዱ ይጠይቁዋቸው፡፡ ተማሪዎቹን ያሳትፉ፡፡

ምንባቡን መሠረት በማድረግ፣ በየትምህርት ክፍሉ የቀረቡትን መልመጃዎች እንደመመሪያቸው ሁኔታ በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን ያሠሯቸው፡፡ ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው፡፡

ምንባቡን ተራ በተራ አንቀፅ በአንቀፅ እንዲያነቡ በማድረግ የተረዱትን ሐሳብ በራሳቸው ቋንቋና የአገላለፅ ስሜት በኢምቋ እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች መልመጃውን ከሰሩ በኋላም እርማት ይስጧቸው፡፡ ተማሪዎችም ጥያቄዎችን በኢምቋ እንዲጠይቁ፣ እንዲመልሱና እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

በቡድን ተከፋፍለው ተማሪዎች የራሳቸውን አጫጭር ተውኔቶች እንዲያቀርቡ ያመቻቹ፡፡ ከተውኔቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጥያቄዎችን በኢምቋ ይመልሱ፡፡ ተውኔቱ የሚስተላልፈውን መልዕክት በኢምቋ እንዲያብራሩ ያድርጉ፡፡

ስነ-ፅሑፍን በተመለከተ ማብራሪያ ይስጡ፡፡ የስነ-ፅሑፍ ዓይነቶችን በምሳሌ መልክ ለተማሪዎቹ በኢምቋ ይግለፁ፡፡ ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገሮች እንዴት እንደሚመሠረቱ በምሳሌ መልክ በኢምቋ ያስረዱ፡፡ በክፍል

ጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ ቁልፍ ምልክቶችን አቻ ቃሎቻቸውን በሰሌዳው በመጻፍ በጣት ፊደላትና በኢምቋ በማሳየት ማጠቃለያ ክለሳ ያድርጉ፡፡

## ማሳሳቢያ

መምህር/ት፣ በዚህ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም የሒሳብ ልውውጥ ለማከናወን በኢምቋ ይጠቀሙ፡፡

## ቁልፍ ምልክቶች፡-

መድረክ፣ ተዋናይ (ትያትር የሚሰራ የጥበብ ሰው)፣ ታሪክ፣ ድርጊት፣ ጭውውት፣ ደራሲ፣ ታዳሚ፣ አዘጋጅ፣ መልዕክት፣ ተውኔት/ትያትር፣ ትዕይንት፣ ድራማ፣ ገፀ ባህርይ

## ማብራሪያ፡-

ተውኔት ከእውነተኛው ዓለም የሚቀዳ ታሪክን መሠረት አድርጎ የሚጻፍ ሲሆን ሰዎች በድራማው ውስጥ የተጠቀሱትን ገጸ ባሕርያት በመወከል ለሕዝብ መድረክ ላይ የሚጫወቱት፣ የሚያሳዩት ትዕይንት ነው፡፡ ሰዎች መድረክ ላይ ከሕዝቡ ፊት ለፊት ሆነው እና ገጸ ባሕርያቱን ወክለው ሲጫወቱ የተወከሉበት ስም፣ ታሪክ እና ባሕርይ የድራማው ስም፣ ታሪክ እና ባሕርይ እንጂ የግለሰቦቹ አይደለም፡፡ ስለዚህ ተውኔት፡- በገሐዱ ዓላም ላይ ተመሥርቶ የሚመነጭ የፈጠራ ሥራ ሲሆን፣ ሰዎች በተውኔቱ የሚሳሉትን ገጸባሕርያት በመወከል በመድረክ ላይ ለሕዝብ የሚቀርብ ትዕይንት ነው፡፡

ተውኔት ሕዝብን ለልማት ለመቀስቀስ፣ ተማሪዎችን በትምህርታቸው እንዲበረቱና ለሃገራቸው ጥሩ ዜጋ እንዲሆኑ፣ ለወጣቶች ከመጥፎ ሱሰኝነት ርቀው ሃገር ወዳዶች፣ ታታሪዎችና ኃላፊነት የሚሰማቸው እንዲሆኑ ለማድረግ ማስተማሪያ፣ ማስጠንቀቂያና ጉዳትን ማሳያ ጥበብ ነው፡፡

በተውኔት ሰዎች የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የሥነ ሥርዓት አከባበራቸውን፣ ሃይማኖታቸውንና እምነታቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ ጥበባቸውን፣ ሙዚቃቸውን፣ የእጅ ሥራቸውን፣ ልምዳቸውን፣ በአጠቃላይ ባህላቸውን ለሌላው የሚያስተዋውቁበት ጥበብ ነው፡፡

**ስነ ቃል፡-** ስነ ቃል ማለት በቃል የሚቀርብ የራሳቸው የሆነ ደራሲ የሌላቸው ህብረተሰቡ በዘወትር ንግግሩ፣ ተግባሩ አኗኗሩ ውስጥ የሚገለግልባቸው የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች ናቸው፡፡

### ጭውውት፡-

» ጭውውት በጓደኛሞች ወይም በሚግባቡ በሁለት ወይም ከሁለት በሚበልጡ ሰዎች

መካከል ይደረጋል።

» ጭውውት ሐሳብ ለሐሳብ መለዋወጥ ነው።

» በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ጭውውት ሊደረግ ይችላል።

» ጭውውት ሲደረግ አንዱ የሌላውን ሐሳብ በጥሞና ማዳመጥ አለበት።

» አንድ ሰው ሃሳቡን ተናግሮ እስኪጨርስ በትዕግስት ማዳመጥ ተገቢ ነው።

» በጭውውቱ ላይ ያልገባን ሐሳብ ካለ መጠየቅ ተገቢ ነው።

መምህር/ት በተማሪው መማሪያ ላይ የቀረበውን ቃለ ተውኔት መሠረት በማድረግ ተማሪዎች ተመሳሳይ ተውኔት በመስራት በክፍል ውስጥ እንዲያሳዩ ያድርጉ።

## መርጃ መሣሪያ

ፎቶዎች/ምስሎች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች/ቻርቶች/ሰንጠረዦች፣ ፍላሽ ካርዶች፣ ሞዴሎች፣ የኢምቋ መዝገበ-ምልክት

## ግምገማ

* የተውኔትን አስፈላጊነትና ጥቅም በኢምቋ ማስረዳት መቻላቸውን ይመልከቱ።
* የተውኔት አካላትን በኢምቋ መገንዘባቸውን ይገምግሙ።
* በራሳቸው መንገድና ፈጠራ አጫጭር ተውኔቶችን ለማሳየት መሞከራቸውን ይከታተሉ።
* ስለተመለከቱትና ስለሚያውቁት ተውኔት መልዕክት በኢምቋ ማብረራት መቻላቸውን ያረጋግጡ።
* የክፍል ጓደኞቻቸው የሚያቀርቡትን ተውኔት ተመልክተው በኢምቋ ሀሳብ መስጠት መቻላቸውን ይገምግሙ።
* በሥዕላዊ መግለጫ የተደገፉ መልእክቶችን በተውኔት መልክ ለመግለፅ መቻላቸውን ይከታተሉ።
* ዐረፍተ ነገሮችን በማሟላት በኢምቋ በአግባቡ ማሳየት መቻላቸውን ይገምግሙ።
* ጥያቄያዊ ዐረፍተ ነገሮችን በኢምቋ ይመሠርታሉ።

# የምዕራፍ አሥር መልመጃዎች መልስ

## ትምህርት ሁለት

### መልመጃ አንድ

1. አምስት
2. መጽሐፍ እና ማስታወሻ
3. ሲያጠና
4. አራቱ
5. እያነበነበ
6. ደስታቸውን ሲገልጹ
7. ደፍተው
8. በሀፍረት አንገቱን ደፍቶ

## ትምህርት ሶስት

### መልመጃ አራት

1. ኤልያስ
2. ጫልቱ
3. ጫልቱ
4. አህመድ
5. ተመስገን
6. ጫልቱ
7. ኤልያስ
8. መስፍን
9. መምህር
10. መምህር

# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የመምህር መምሪያ

# 5ኛ ክፍል

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር